# የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አመሠራረት

የአገራችን የመንግሥት ታሪክ በጽሑፍ መያዝ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የአስተዳደር ሥሪቱ እንደ አውሮፓ አህጉር የጉልተኛ ሥርዓት ነበር። በዚህ ሥርዓት የሚገዛው ንጉሥ የሕዝቡን የሥልጣን የበላይነት የማይቀበልና የአንድን ሰው በሕግ ያልተገደበ ሥልጣን የሚያንጸባርቅ ቢሆንም፤ የቤተሰባዊነትና አንድ የመሆን ስሜት ስለነበረው አገዛዙ ብዙም አይከፋም ነበር። አመጣጡ እንዴት ነው ሲባልም አንዱ የዘር ሐረግ ቆጥሮ ሲመጣ፣ ሌላው በመሣሪያ ኃይል አስገብሮ ሆኖ ይገኛል። የዘር ሐረግ የቆጠረውም ሆነ በመሣሪያ ኃይል አስገድዶ ሥልጣን የያዘው ዞሮ ዞሮ በእግዚአብሔር እንደተመረጠ ስለሚቆጠር ኅብረተሰቡ ይህንኑ አምኖ በመቀበል ሰጥ ለጥ ብሎ በቅብብሎሽ ሲገዛ ኖሯል። በዚሁ የዘውዳዊ ሥርዓት ከንጉሡ በመቀጠል ሥልጣኑን በተዋረድ የሚይዙት ፌዴራላዊ ይዞት በነበረው በአምባ ባላባቶች የራስ ገዝ ሥርዓት ነበር። ዐፄ ኃይለ ሥላሴም ወደ ሥልጣን የመጡት በዚሁ መንገድ ነበር፤ በጠላት ወረራ ተቋረጠ እንጂ።

ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን በሥልጣኔ ለማሳደግ ብርቱ ፍላጐት ነበራቸው። ሥልጣን በያዙበት ወቅት የነበረው የአገሪቱ ሁኔታ ግን ምኞታቸውን ለማራመድ የማያስችሉ ሁለት ችግሮች ደንቅሮባቸው ነበር። አንደኛው ከዐፄ ምኒልክና ከልጅ ኢያሱ መንግሥት የተላለፉ ታላላቅ መሳፍንትና መኳንንት በመንግሥቱ አመራር ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው መሆኑ፤ ሁለተኛው አብዛኛዎቹ በቂ የታጠቀ ኃይል ስለነበራቸው፣ ቢያምጡ በመንግሥቱ ላይ ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ግንዛቤ መኖሩ ነበር። በወቅቱ፣ ለንጉሡ ቀራቢና አማካሪ ከነበሩት ከፈረንሣዮችና ከቤልጂጎች ባገኙት ምክርና ራሳቸውም የፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆናቸው የአውሮፓን ታሪክ ባወቁት መጠን ለመንግሥታቸው አቋም መጥናት የሚያስቡትን አስተዳደር ለመትከል ይሹ ነበር። አነሳሳቸውም ከላይ የተጠቀሱትን ጠንካራ መሳፍንት፣ መኳንንትና የጦር አበጋዞች ኃይላቸውን አዳክሞ ያለተቀናቃኝ መንግሥቱን መምራት ነው። ይህንንም ለማድረግ እያንዳንዳቸው ከራሳቸው መጠበቂያ ጥቂት ሰው በቀር ሠራዊታቸውን እንዲያሰናብቱ፤ ባንጻሩም፣ በሚበተነው በመሳፍንቱና በመኳንንቱ ሠራዊት ምትክ በማዕከላዊ መንግሥት የሚመራ ቋሚ አገር ጠባቂ ጦር ማቋቋም ነበር። ከውጪ አማካሪ ሰዎች ባገኙት ምክር ተመሥርተው ያደረጉት ነው የሚባለውና መሳፍንቱና መኳንንቱ በሠራዊታቸው ብዛት መሠረት አስፋፍተው የያዙትን የከተማ ቦታ በየስማቸው ተለይቶና ካርታ ተነሥቶ ልኩ እንዲታወቅ መደረጉም ሌላው ውጥናቸውን ዕውን ለማድረግ የዘየዱት ነበር። የድልድሉ ዝርዝርም እንደሚከተለው ነበር።[11]

---

[11] ስለዚህ ታሪክ ብዙ ይወራ ስለነበር ማስረጃ ሳፈላልግ፤ የአንድ አካባቢ ሰዎችና ወዳጆች ከነበርነው አቶ ታጀበ በየነ በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. በስደት ይኖር ከነበረበት ከካናዳ እንደመጣ እንኳን ለአገርህ አበቃህ ልለው እንግሊዝ ኤምባሲ ፊት ለፊት ካለው ቤቱ በሔድኩበት ኢጋጣሚ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የሕዝብ

፩ኛ ራስ ካሣ ኃይሉ
፪ኛ ራስ ብሩ ወልደ ገብርኤል
፫ኛ ራስ ልዑል ሰገድ አጥናፍሰገድ
፬ኛ ራስ ጌታቸው አባተ
፭ኛ ራስ ናደው አባወሎ
፮ኛ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት
፯ኛ ራስ ከበደ መንገሻ
፰ኛ ራስ ዳርጌ ሣህለ ሥላሴ
፱ኛ ራስ ተሰማ ናደው
፲ኛ ደጃዝማች ውቤ አጥናፍሰገድ
፲፩ኛ ደጃዝማች አያሌው ብሩ
፲፪ኛ ደጃዝማች ገነሜ
፲፫ኛ ደጃዝማች ዘውዴ
፲፬ኛ ደጃዝማች ይመኑ
፲፭ኛ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ
፲፮ኛ ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኑኤል
፲፯ኛ ደጃዝማች ይገዙ በሐብቴ
፲፰ኛ ደጃዝማች ማተቤ ... ወዘተ. ነበሩ::



*የመሬት ድልደሉ ካርታ*

ንጉሡም የምክሩን ጠቃሚነት ተገንዝበው እንደምክሩ እንዲፈጸም፣ ለመሳፍንቱ፣ ለመኳንንቱና ለጦር አበጋዞቹ የራስ መጠበቂያ ጥቂት ሰው ብቻ አስቀርተው ሠራዊቶቻቸውን እንዲያሰናብቱ ትእዛዝ መስጠታቸውን ተከትሎ፤ አብሮ በልቶ፣ ጠጥቶ፣ ተፈቃቅሮ፣ ችግርና መከራውን ደስታና ሐዘኑን በጋራ ተካፍሎ አብሯቸው ሲዘምት ታማኝነቱን፣ ጀግንነቱንና ቁርጠኛነቱን

---

*ግንኙነት ክፍል ኃላፊ ስለነበር መጽሐፍ ልጽፍ ስለሆነ ስለ አዲስ አበባ ከተማ አመሠራረት መረጃ እንዳለህ ብትሰጠኝ ብየ በጠየኩት መሠረት የሰጠኝ ነው። አቶ ታደሰ በየነ በሙት ባልሞላ ጊዜ ሞተ። የካርታውን የወሰን መሠመር ያሳላኝ የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት ነው። ካርታውን ለማተሳት የረዱኝን የካርታ ሥራ ድርጅት የካርቶግራፊ ክፍሉን ሠራተኞች አመሰግናለሁ::*





የመሬት ድልድሉ ካርታ

*ከፊትህ ሙቼ ይብላኝ አሞራ፤*
*ግዝት ያርግብኝ ሞት እንዳልፈራ*


እያለ ለጌታው የነበረውን ታማኝነት፣ ፍቅርና አክብሮት እያረጋገጠ፣ ጀግኖ እያጃገነ፣ የኖረ ሎሌ፤ በጁ በነበረው መሬት የተጋሪነት መብቱ ተገፎ ያለምንም መተዳደሪያ ተበተነ። በዚህ መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ ቦታ ከአራት የሦስት እጁ ባለቤት የሆኑት እነዚህ መሳፍንት፣ መኳንንትና የጦር አበጋዞች ከተማው እየሰማ ሲሔድ መሬቱን ሸንሽነው እየሸጡ መክበርና ገንዘብ ባንክ ማስቀመጥ ጀመሩ። አብሯቸው ሲወድቅ ሊነሳ የነበረው ሠራዊት የመሬት ተጋሪነት መብቱ ተገፎ ተበተነ። በተበተነው የመሳፍንትና የመኳንንት ጭፍራ ምትክም በሆለታ ገነት አገር ጠባቂ ጦር ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ተቋቁሞ በዘመናዊ ወታደር ሙያ ማሠልጠን ተጀመረ።

ሌላው ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ላሰቡት የለውጥ ውጥን ተጋርጦባቸው የነበረው ችግር አገሪቱን የዘመናዊ አስተዳደር ፈር ለማስያዝ የሚያስችል በወቅቱ የነበሩትን እነዚህን ባለ ሥልጣኖች የሚተካ በቂ የተማረ ሰው አለመኖር ነበር። በመሆኑም የተማረ ሰው ማፍራት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ስለሆነ፤ በዚያን ጊዜ በክፍለ አገር በግዛትነት ይታወቁ በነበሩ በጠቅላይ ግዛቶች የሚገኙ ገዥዎችና ስመ ጥር ባላባቶች በያሉበት ቢያንስ አንድ አንድ ዘመናዊ ትምህርት ቤት እንዲያሠሩ፤ ማሠሪያ ገንዘብ የሚያጥራቸው የመንግሥትን ድጋፍ እንዲጠይቁ በማበረታታት ሥራው ተጀመረ። የአገሪቱን ሥልጣኔ ለማፋጠንም የማይናቅ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ተላኩ። አዝጋሚ ቢሆንም ሒደቱ እንዲህ ቀጥሎ በየጠቅላይ ግዛቱ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ተከፈተ። ሀብታምና ድሃ፣ ዘር፣ ሃይማኖትና



*ከዳግማዊ ምኒሊክ ት/ቤት ለትምህርት ወደካይሮ የተላኩ ወጣቶች*

ጾታ ሳይለይ ማንኛውም ዕድሜው ለትምህርት የደረሰ ሁሉ ገብቶ እንዲማር በሩ



*ለዳግማዊ ምንሊክ ት/ቤት ለትምህርት ወደካይሮ የተላኩ ወጣቶች*

ጾታ ሳይለይ ማንኛውም ዕድሜው ለትምህርት የደረሰ ሁሉ ገብቶ እንዲማር በሩ

ለሁሉ ክፍት ሆነ:: ነገር ግን በነበረው የሕዝብ ግንዛቤ ወደ እንደዚህ ያሉ ትምህርት ቤቶች መግባት የሃይማኖት ለውጥ ያመጣል በሚል የወላጆች ጥርጣሬ ትምህርት ቤቶቹ በቂ ተማሪ ማግኘት አልቻሉም:: ችግሩን ለመፍታት ብዙ ሰበካ ከማካሔድ አልፎ ራስ ተፈሪ (ኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ) ባንዳንድ ቦታ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ የማበረታቻ ስጦታ ያደርጉ ነበር ይባላል:: በዚህ መልኩ ተማሪ ቤት ገብተው የሚማሩ ወጣቶች ቁጥር መጨመር ቢጀምርም፣ በጠላት መምጣት ይሄኛውም ውጥን ተደናቀፈ::

የጠላት ወረራ ዕውን ሆኖ የማይጨው ዘመቻ የክተት ጥሪ ሲታወጅ የሚያስተዛዝብ ቀውጢ ቀን መጣና እነዚያ መኳንንትና የጦር አበጋዞች ወደ ማይጨው ለመዝመት ያን የበተኑትን ሎሌ እንደገና ለመሰብሰብ በመብራት ማፈላለግ ጀመሩ:: ይህን የሰማው ከተበተኑት ሎሌዎች አንዱ

*አይመጡም ስትሉ ይኸውና መጡ*
*ሎሌ ገንዘብ አይደል ከባንክ አታወጡ*

በማለት ይህቺን ስንኝ በቀረርቶ ለታሪክ ትቶ፣ ያገር ጉዳይ በመሆኑ በየጌታው ተሰብስቦ በመንግሥት ከሚታዘዘው ጦር ጋር ወደ ዘመቻው ተመመ:: የአገሪቱ ሀብት፣ ዕውቀትና ጉልበት በሙሉ ወረራውን ለመከላከል ዋለ:: ለአገሩ ነፃነትና ዳር ድንበር መከበር ወደ ዘመቻ ከሔደው መኳንንትና ሠራዊት ብዙ ተሰዋ:: በመጨረሻም የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ወድቆ የጠላት ጦር በየጠቅላይ ግዛቱ ገባ:: ድሉ ቀንቶት የገባው የጠላት ኃይል አገር ውስጥ እንደገባ ከፊሉ በአስተዳደር ዘርፍ፣ ከፊሉ ለሠራዊቱ እንቅስቃሴ በሚያመች የሥራ ዘርፍ፣ በመንገድ ሥራ፣ በስልክ፣ በመብራት፣ በውሀ መስመር መዘርጋት እና በሠፈር ግንባታ...ወዘተ. አተኰረ::

ሆኖም፣ አርበኛው ጠላት ባለበት አካባቢ ሁሉ ዘልቆ እየወጋ ሲያስጨንቀው የልማት ማካሔጃ መሣሪያውን ጥሎ ጠበንጃውን እያነሳ በመከላከል ሣይረጋጋ አምስት ዓመት በጦርነት ቆየ:: በዚህ ጊዜ ከእርሱ ጋር በረዳትነት የሠሩ ወጣቶችና ሌሎች በአስተዳደርና በፖለቲካ ለጠላት ማገልገላቸው ቢያሳዝንም፣ የቀሰሙት ልዩ ልዩ ሙያ ከጠላት መልቀቅ በኋላ ለአገር ግንባታ አጋዥ የሙያ ሥራ እንደሚሆን ታመነ:: ስለዚህ፣ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ገና ከኢትዮጵያ ግዛት ድንበር እንደደረሱ፣ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ.ም፣ "ወርቃማ ዐዋጅ" የተባለውን አገር አቀፍ የእርቀ ሰላም ዐዋጅ ዐወጁ[12]:: በዚህ ዐዋጅ ባንዳና የውስጥ አርበኛ፣ ያለፈ በደላቸው ሁሉ በምሕረት ታልፎ ሁሉም ባላቸው ዕውቀትና ችሎታ በአዲሱ የአገር ግንባታ ሥራ እንዲሳተፉ መብት ተሰጠ:: ዐዋጁም ንጉሡ ከሠሯቸው ታላላቅ ሥራዎች አንዱ ተብሎ የሚጠቀስ ሆነ::[13] በፖለቲካና በአስተዳደር ጠላትን ከረዱት መካከል ይልማ ደሬሳ በኋላ በኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የገንዘብ ሚኒስትር፣ መኮንን ደነቀ በኋላ በአገር

---

[12] የሕዝብ ማስታወቂያ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፩ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ.ም.
[13] ፍሬ ከናፍር ቁጥር ፩ ፲፱፻፴፫ ዓ.ም.

ግዛት ሚኒስቴር የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ሚኒስትር ደኤታ፣ አምደሚካኤል ደሣለኝ በኋላ የማስታወቂያ ምክትል ሚኒስትር፣ ከበደ ሚካኤል በኋላ የትምህርት ምክትል ሚኒስትር፣ እሸቴ ገዳ በኋላ አፈ ንጉሥ በአገር ግዛት ምክትል ሚኒስትር ሆነው መንግሥትን ያገለገሉትን መጥቀስ ይቻላል። ሌላው ቀርቶ በአገር እንቀራለን ያሉ ጣሊያኖችም ቀርተው ባላቸው ልዩ ልዩ የእጅ ጥበብ ሠርተው እንዲተዳደሩ ተፈቀደላቸው። ይህ አገር አቀፍ ዕርቀ ሰላም ዐዋጅ የአርበኛውን ክፍል ቢያሣዝንም፣ ለአገር ግንባታ ጠቃሚ ሆኗል። አርበኛው ግን በእጅጉ ስለተከፋ ቅሬታውን የምትገልጽለትን፣

*ኢትዮጵያ አገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ*
*የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ፤*

ብሎ ተቀኘ።



*ባላታ ታከለ ወልደ ሐዋርያት*

ይህ ዐዋጅ ባይታወጅ ኖሮ ከነፃነት መመለስ በኋላ አርበኛውና ባንዳው በቂም በቀል ተያይዞ ከፊሉ በጉልበት እየተበቀለ፣ ሌላው ሊበቀልም እያለ፤ ይህን አድርጎኛል፣ ይህን በድሎኛል ብሎ ለመካሰስ ማለቂያ በሌለው ሙግትና ክርክር ብዙ አምራች የሰው ጉልበትና እውቀት ሥራ ይፈታ ነበር። አዲሱን መንግሥትም ከማይወጣው አረንቋ ውስጥ ከቶ ያላቁጠው ነበር።

ዐዋጁ አርበኛውን ግን አስከፍቷል። ስለዚህም ከእንግዲህ አገሪቱን የሚያስተዳድር ደሙን ያፈሰሰላት፣ አጥንቱን የከሰከሰላት የቁርጥ ቀን ልጇ አርበኛው እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም በማለት ፅኑ አቋሙን በማሳወቁ፤ ነፃነት እንደተመለሰም በቁጥር አነስተኛ ቢሆንም በዓይነቱ ከፍተኛ የሆነው ስደተኛው አቋሙን ከአርበኛው ጋር አድርጐ አርበኛውን አጠናከረ። ቀደም ብሎ በነደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ተቀስቅሶ የነበረው *ያፈረሰ ቂስ ተመልሶ አይቀድስ፣ የሸሸ ንጉሥ ተመልሶ አይነግሥ* የሚለው መግለጫ አርበኞች በነበሩበት ሁሉ ተዳርሶ ስለነበር ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ መናገሻ ከተማው ሲገቡ ሕዝቡ አንድ ላይ ሆኖ "ወደ ዙፋን አይመለሱም" ይል ይሆናል ተብሎ ተሰግቶ ነበር። የሆነው ግን በተገላቢጦሽ የሕዝቡ ኃይል ተከፋፍሎ የተለያየ አቋም አንጸባረቀ። በአንድ ፊት የቀድሞዎቹ የአገሪቱ ጉልተኞች የአገሪቱ የአስተዳደር



ብላታ ታከለ ወልደ ሐዋርያት

ኃላፊነት እንደ ቀድሞው የዘር ሐረጋቸውን በሚመዙ የበላይነት መቀጠል አለበት ብለው ቆሙ። ከፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ በፊት በኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበረው አገዛዝ ተጠሪነቱ ለንጉሠ ነገሥቱ ሆኖ የመሳፍንት የአካባቢ የራስ ገዝ ሥርዓት ነበር። በየአርበኝነቱ ቀጣና በአርበኝነት ሲፋለሙ ከነበሩት ውጪ በወረራው ጊዜ በረሃ ገብተን ከጠላት ጋር ግንባር ለግንባር ተሰልፈን ባንዋጋም ውስጥ ለውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚፈለግብንን የአገር ነፃነት ትግል ግዴታ ተወጥተናል ባይ የውስጥ አርበኞች የሚል መጠሪያ የተሰጣቸው ወገኖች ደግሞ መጡ። ከዚህ በተፃራሪ ከአሁን በኋላ አገሪቱ መተዳደር ያለባት በተማሩና ችሎታ ባላቸው እንጂ በሌላ መንገድ መሆን የለበትም የሚሉ የተማረው ክፍል ወገኖችም በመነሳታቸው መለያየቱ ለንጉሡ ያላሰቡትና ያልጠበቁት ከሰማይ የወረደ በረከት ሆነላቸው።

በዚህ የተነሣ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን በአዲስ የሥልጣኔ መንገድ ለመምራት ግንቦት ፬ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. በወጣ የመንግሥት ማስታወቂያ (ነጋሪት ጋዜጣ) አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስን የትልቁ (የደረቁ) ማኅተም ጠባቂ አድርገው ሾሟቸው[14]። ከዚህ ጋር በማያያዝም የአዲሱን መንግሥት ሥሪት (የአስተዳደር መዋቅር) እንዲያዘጋጁ አዘዙ። በትዛዙም መሠረት፡- በ፲፱፻፴፭ ዓ.ም. ጳሐጉሜ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ መንግሥት ሥሪት (መዋቅር)፤ ሕግ አወጭ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈፃሚ በሚል በሦስት ዘርፍ የተከፈለ አወቃቀር ኖሮት ዘመናዊ ማዕከላዊነትን የጠበቀና ያጠበቀ ጠፍንጐ የሚይዝ ቀጣይነትን የሚያረጋግጥ መዋቅር ቀርፀው በሥራ ላይ ለማዋል ንጉሡን አሳይተው ይሁንታን አገኙ። ሹመቱ የሚሰጠው በንጉሠ ነገሥቱ ይሁን እንጂ በአብዛኛው ከላይ እስከ ታች (ከጠቅላይ ሚኒስትር እስከ ወረዳ ገዥ) በዘርፍ የሚደለደሉ ባለሥልጣኖችን የመመልመሉና ደልድሎ ለሹመት የማቅረቡ ሥራ የጸሐፌ ትእዛዝ ብቻ ነበር። ይህም ሲባል የንጉሡ ቅድመ ዕውቅና ሳይኖር ማለት አይደለም። እንዲህ በመሆኑ በአካባቢ ተወላጅነታቸው ተሰሚና ተከባሪ የነበሩትን የየጠቅላይ ግዛቱን መሳፍንት መኳንንትና ባላባት አገር ገዥዎች፣ በሳቸው አባባል "ካባ አጣፊዎችን" የመንግሥት ተቀናቃኝ እንዳይሆኑ አደረጉ። ይህንን ለማድረግም ‹‹ካባ ጣፊዎች›› የሚሏቸውን ከትውልድ አገራቸው ቀስ በቀስ እያነሱ ወደ አዲስ አበባ አምጥተው ሥልጣንና ጉልበት በማሣጣት አብዛኛውን የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል፣ ከፊሉን ደግሞ በዳረጎት ተዳዳሪ ደጀጠኝ በማድረግ ያለመንግሥት ፈቃድ ከአዲስ አበባ የማይወጡ አደረጉ። እገዳው ተቀናቃኝ ይሆናሉ ተብለው የሚጠረጠሩትን ሁሉ ያጠቃለለ ስለነበር፤ በዚህ ከተከፉት ውስጥ አንዱና የመጀመርያው የኢትዮጵያን የብር ኖት የሳሉት ታዋቂው ሠዓሊ አገኘሁ ዕንግዳ[15]


*ከመሸ ተነሳሁ ከተፈታ በሬ*
*እደርስ አይመስለኝም ከእንግዲህ አገሬ።*

---

[14] ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፩ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ.ም.

[15] የአማርኛ ሰዋሰው መማሪያ በብላታ መርስዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ

የማለት በወቅቱ የተቀኙትን ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የአማርኛ ሰዋስው መማሪያ በተባለው መጽሐፋቸው ላይ አስፍረውታል። በምትካቸው ለመንግሥት ታማኝና የጸሐፊ ትዕዛዙን ፈቃድ የሚፈፅሙ በአብዛኛው የአገሩ ተወላጅ ያልሆኑና ሕዝብ የኛ ነው ብሎ የማይቀበላቸውን እየሾሙ ላኩ።



*ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ*

ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ የቀረፁት ዘመናዊ የመንግሥት አስተዳደር መዋቅር ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈፃሚ ዘርፍ ያለው ሆኖ፤ የሕግ አውጪው አካል ሁለት ክፍሎች ነበሩት። እነሱም የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት እና የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ናቸው። የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሆነው የሚገቡት በሕዝብ ምርጫ ሳይሆን፤ መሳፍንት፣ መኳንንት፣ ባላባቶችና ቆየት ብሎ ደግሞ ከተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሥራ የተነሡ ሰዎች በሹመት ነበር። የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ የተያዘው እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በመሆኑ፣ ስለምክር ቤቱ የሥራ ኃላፊነት በቂ ግንዛቤ አልነበራቸውም። አብዛኛዎቹ የመወሰኛው ምክር ቤት አባላት ሕጎችን ለማፍለቅ ብቃቱ የሌላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ፤ የተዘረጋው ሥርዓት ከአስፈፃሚው ክፍል የተላከን የሕግና የደንብ ረቂቅ ወይም ከውጭ መንግሥት ጋር የሚደረግ ስምምነትን ... ወዘተ. ዓይቶ ከማጽደቅ ያለፈ ስለአገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ማኅበራዊ ጉዳይ አንሥቶ መክሮ የሚያለማና የሚያሠራ ደንብ ለማውጣት መብትም ችሎታም ያልነበራቸው ናቸው።


የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባሎችም መጀመሪያ ከየጠቅላይ ግዛቱ ባላባቶችና የታወቁ ሰዎች በመንግሥት መራጭነት የሚሠየሙበት አካል ነበር። ኋላ በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. በተሻሻለው ሕገ መንግሥት መሠረት የሕግ መምሪያ ምክር ቤቱ በሕዝብ በተመረጡ አባላት ይሠራ ጀመር። ይህም ሆኖ፣ የሕግ መምሪያው ምክር ቤት እንደ ሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ከሕግ አስፈፃሚው ክፍል የተላከውን የሕግ፣ የውልና ... ወዘተ. ረቂቆችን የሚያፀድቅ ውይይት ከማድረግ ያለፈ በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መክሮ፤ ችግር የሚፈታ፣ አገር የሚያሳድግ፣ ሕዝብ የሚያበለፅግ ሐሳብ ለማመንጨት ወይም ሕግ አውጥቶ ለማሠራት፣ ወይም የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ጠርቶ የመጠየቅ ብቃትና ሥልጣን (በሕገ መንግሥቱ ስለተገደበ) አልነበረውም። ስለዚህ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባሎች ተመርጠው



ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ

መጥተው የሚያገለግሉበትን ጊዜ ጨርሰው ከመሔድ ያለፈ አጥጋቢ የሚባል ሥራ አከናውነዋል ለማለት አያስደፍርም።

በሕግ አስፈፃሚው በኩል ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ቀደም ብለው በቀረፁት መዋቅር መሠረት የሕግ አስፈፃሚውን ክፍል በየዘርፉ በደለደሏቸው ባለሥልጣኖች ሲያካሒዱ ቆይተው፤ ደጃዝማች መኮንን እንዳልካቸው በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. ቢትወደድ ተብለው ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆኑ፤ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ በያዙት ሥራ ላይ የአገር ግዛት ሚኒስትርና የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መምሪያ ኃላፊነቱን በመደረብ የሕግ አስፈፃሚውን ዘርፍ እስከ ፲፱፻፵፮ ዓ.ም. ድረስ መርተው ከፈለጉት ደረጃ አድርሰውታል። የሕግ ተርጓሚው ክፍልም በአዲሱ የመንግሥት አስተዳደር መሆን


ሚስተር ናታን ማሬይን

እንደሚገባው ያልሆነ ተቋም ነበር። ይህን ለማስተካከል ጸሐፌ ትእዛዝ ከ፲፱፻፴፫ እስከ ፲፱፻፵፮ ዓ.ም. በተደራቢነት ይዘውት የነበረውን የአገር ግዛት ሚኒስትርነቱን ሥልጣን ለቀው በዚያው ዓመት የፍርድ ሚኒስትርነቱን ሥልጣን ደርበው በመያዝ የኢትዮጵያን መንግሥት ሕግና ሥርዓት ዘመናዊ ለማድረግ በሕገ ሥርዓቱ ላይ በምክርና በሥራ የሚያግዙ የውጭ አገር የሕግ ባለሙያዎችን በመያዝ ለመሥራት ሞክረው ነበር። በዚህ ረገድ በዳኝነት ጆጅ ግራቫውስኪ (የእንግሊዝ ዜጋና የፖላንድ ተወላጅ)፣ ጆጅ ኖርድስትሮን (እንግሊዛዊ)፣ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግነት ደግሞ ሚስተር ናታን ማሬን[16] (እሥራኤላዊ የእንግሊዝ ዜጋ ቀደም ብሎ በኢሩሳሌም ኢትዮጵያ ገዳማት ንብረት ጉዳይ ጥበቃና ነገረ-ፈጅ ሆነው ያስከብሩ የነበሩት)ን ይዘው ቢሠሩም እንደፈለጉት አልሆነላቸውም። ዋናው ችግር የፍርዱ ሒደት እጅግ የተንተተና የተንዛዛ መሆኑ ነበር።[17] ስለዚህም የፍርድ ሒደት (ፍትህ) በኢትዮጵያ ጠፍቶ ነበር ለማለት አስደፍሯል።

[16] ሚስተር ናታን ማሬን በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥቱን ከፍተኛ ተዋንያን ናቸው የተባሉትን ሰዎች ክስ የመሠረቱና የዚህ ታሪክ ጸሐፊ ክስ ላይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ የሕግ ግድፈት አለበት፤ ተከሳሹ ባልተከሰሰበት አንቀፅ ሳይሆን በተከሰሰበት አንቀፅ ፍርዱ ይስተካከል፤ ብለው ለጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ደብዳቤ የጻፉ ናቸው። የደብዳቤው ፎቶ ኮፒ በምዕራፍ ፫ ከፍርድ ቤቱ ጉዳይ ጋር ተያይዟል። ጉዳዩ ትልቅ የመብት መጠበቅን ግዴታ እንደሚገልጽ ልብ ይሏል።

[17] ምክንያቱም የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ መሪዎች ወደእንቅስቃሴው ለምን እንደገቡ እንደምናየው ማንኛውም የፍርድ ሒደት የተንዛዛና ረዥም ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ "የዘገየ ፍርድ እእንደተነፈገ ይቆጠራል" የሚለውን መርህ ፍፁም የዘነጋ ነበር።



ሚስተር ናታን ማሬይን

ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከ፲፱፻፴፫ እስከ ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. ድረስ እራሳቸውንና ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስን ብቻ የሁሉ ጉዳይ ወሳኝ በማድረጋቸው፣ ለሕግ ተርጓሚው ብዙ ትኩረት እንዳልተሰጠበት ከአሠራሩ ሒደት ይታያል። በዚህ ሥርዓት ከላይ እስከታች በየዘርፉ ለሚደለደሉ ባለሥልጣኖች ተካይም ነቃይም ዐፄ ኃይለ ሥላሴና ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ብቻ ነበሩ። በእርግጥ በአጠቃላይና በአንጻራዊ አነጋገር መንግሥታዊ አወቃቀሩ በአገሪቱ ሰላምን ለማስፈንና የመንግሥቱን ዕድሜ ለማራዘም ሲባል የተቀረፀ ሥርዓት እንደመሆኑ ዐላማው ግቡን መቷል ማለት ይቻላል። የዐፄ ኃይለ ሥላሴና የጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ስምምነት ግን እስከመጨረሻው የዘለቀ አልሆነም። ዐፄ ኃይለ ሥላሴና ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ከ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. እስከ ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. ድረስ ዐላማቸውና መንገዳቸው አንድ ነበር። ከ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. በኋላ ግን መንገዳቸው መፈርቀቅ (መሠንጠቅ) ጀመረ። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መጀመሪያ አስበው ተነስተውበት የነበረው አስተዳደርን የማሻሻልና አገር የማሳደግ ፍላጐት በረደ። ተሿሚዎች እንደቀድሞው የአሰበ ተፈሪና የሚዛን ተፈሪ አውራጃ ገዥዎች በችሎታና በብቃት ተመርጠው መሾማቸው ቀርቶ ወደጥንቱ ሥርዓት መመለስ ያዘ። የአቋም ልዩነቱ የመጣው ወልደ ጊዮርጊስ ተጀምሮ በነበረው መንገድ አዲስ ተሿሚዎች መጣቶችና የተማሩትን እንዲያካትት የሚፈልጉ ሲሆን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ደግሞ ሹመቱን የሥልጣን ዘመናቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ ያለተቀናቃኝ ለማስቀጠል ለሚችሉ በእምቻ፣ በጋብቻ፣ በዝምድናና በጥቅም ለተሣሠሩ ታማኞች ለመስጠት በመፈለጋቸው ነበር። በዚህ ሁኔታ "ጠብቀኝ እጠብቅሃለሁ" የራስ ወዳድነት ባሕርይ ተቀዳሚ ዐላማ ሆኖ የሕዝብ የኑሮ ዕድገትንና የአገር መሻሻልን ቀዳሚ ዐላማ ያላደረገ አመራር እንዲሰፍን ሆነ። ይሁን እንጂ ሁለቱም ይህን የአመለካከት ልዩነታቸውን በውስጣቸው ይዘው በመቻቻል የመሾም የመሻር ሥልጣኑን በእጃቸው አድርገው ቀጠሉ።

የሚተክሉት እነሱ እንደመሆናቸው የሚነቅሉትም እነሱ ብቻ ነበሩ። ስለዚህ ተሿሚው ሁሉ በእነርሱ በጐ ዓይን እንዲታይና ከሥልጣኑ እንዳይወርድ ተጠንቅቆና እነሱ ከሚጠሉት ነገር ሁሉ ርቆ በመልካም መዝገባቸው ውስጥ ያለ እንዲሆን ይጥር ነበር። እንዲህ በመሆኑም በዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አስተዳደር ዘመን አንድ ባለሥልጣን ሕዝቡን በአስተዳደር በድለሀል፣ ፍትሕ አጓድለሀል፣ የሕዝብ ሀብት መዝብረሃል፣ በሥልጣን ባልገሃል፣ ተብሎ ከሥልጣን የወረደ ወይም ተከሶ በሕግ የተቀጣ አልነበረም። ተደረገ የተባለ ቢኖር በጉዳዩ ስማቸው ከተነሳ ሰዎች አንዳንዱን ከነበረበት ወደ ሌላ ቦታ ማዘወር ነበር። ኋላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪዎች የእንዳልካቸው ካቢኔን በዐደባባይ ለመተቸት *"ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም"* ማለት እንደተቀኙት።

በእንዲህ ዓይነቱ አስተዳደር ላይ ቀስ በቀስ የሕዝቡ ንቃተ ኅሊና እያደገ፣ የተማረው ሰው ቁጥር እየጨመረ ሲሔድ ጥያቄና ነቀፋ እየበረከተ መምጣቱ አልቀረም። በዚህ ጊዜ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እና ጸሐፊ ትእዛዝ እየቀደማቸው የሔደውን የሕዝብ የዕድገት እርምጃና ጥያቄ ተገንዝበውና ከሕዝብ ፍላጎት ጋር አጣጥመው

መምራት እያቃታቸው ስለሔደ ዙፋኑ መዝመም ጀመረ። በሌላ በኩል ደግሞ ጸሐፌ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ በጣም የገነኑ፣ የተከበሩና የተፈሩ ስለነበሩ የሥልጣን ፍላጎት ሊመጣ ይችላል የሚል ጥርጣሬ በብዙ ሰው ሐሳብ ላይ ገባ። በተለይ አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ "ይህ ሰውዬ በጣም እየገነነ ሒዷል፤ ጉልበቱ ገዝፏል፤ ለመንግሥቱ ያሰጋል፤ አይሆንም፣ ይነሣ ብለው" መወትወታቸው ይነገራል። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ እንግሊዝ አገር ለጉብኝት ሔደው በነበሩበት ጊዜ እንግሊዞቹ ቀጣዩን መሪ ቅረበው ተገናኘው (Meet the next leader) የሚል ብሒላቸው ተደጋግሞ ሲነገር፤ ጃንሆይ እንዲሰሙት ተደርጓል ይባላል። ከዚያ በኋላ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በጸሐፌ ትእዛዝ ላይ የነበራቸው አመኔታና ቀረቤታ እንደ ብላቴን ጌታ ኅሩይ እየመነመነ መጣና ወልደ ጊዮርጊስን የሚያህል ታማኝ አገልጋይና የኢትዮጵያ መንግሥት አስተዳደር ዋልታና ምሰሶ ታላቅና ብርቱ ሠራተኛ ሰው ክብራቸውን ቀንሰውና ደረጃቸውን አውርደው ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች በቆዳ ስፋት አነስተኛ ወደሆነው አርሲ ጠቅላይ ግዛት ገዥ አደርገው ከግቢ አወጧቸው። ጸሐፌ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ከ፲፱፻፳ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ፲፱፻፵፮ ዓ.ም. ድረስ መጀመሪያ የራስ ተፈሪ፤ በመቀጠልም የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ደጋፊ አድራጊ ፈጣሪና ወሳኝ ባለሥልጣን ነበሩ።

የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የመሻሻል እርምጃ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሔዶ ጭራሽ ኅታችነቱ እያመዘነ ሔደ። ነገሩም የሆነው እንዲህ ነው። ንጉሠ ነገሥቱ የተማረ ሰው ፈለጉ፤ መጣ። ከዚያም በንፍገት ለራሳቸው የያዙትን ሥልጣን መካፈል ፈለገ፤ ይሄኔ ከማንም በላይ ተራማጅ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት የዕድገት ለውጥ ጠያቂውን መቃወም አመጡ። ይወዱ የነበሩትን ሁሉ ጠሉ። ይወዳቸው የነበረውም ሁሉ በተለይም ወጣቱና የተማረው ክፍል ጠላቸው። በአመራሩ ውስጥ ያሉትን ባለሥልጣኖች ተጠያቂ የማያደርግና ሥልጣናቸውን የሚገታ የሕግ ገደብ ወይም እንደጊዜው የሚሻሻል የሥራ መመሪያ ስላልነበረ ባለሥልጣኖቹ እንዳሻቸው በማስተዳደር ሕዝቡን ለድህነት፣ ለድንቁርና፣ ለጥላቻና ለምሬት ዳረጉት። በዚህ አመራራቸው ንጉሡ ሕዝቡን አስከፍተውና አስመርረው የመንግሥታቸውን የውድቀት በደል አሳድገው ከመውደቂያ አፋፍ አደረሱት።[18] ስለዚህም በተለምዶ «የታኅሣሥ ግርግር» የሚሰኘው የንጉሡን አስተዳደር ለመለወጥ ያቀደ መፈንቅለ መንግሥት እንዲካሔድ ምክንያት ሆነ።

[18] ይህን አስመልክቶ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች በደሉን በዝርዝር ገልጸዋል። የዘውድ ጠባቂውና የንጉሠ ነገሥቱ ታማኝና ቀራቢ የነበሩ ስምንት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችም ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበዋቸው የነበሩ ማስታወሻዎች (በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ክፍል በአባሪነት ተያይዘዋል) ከፍተኛ ባለሥልጣኖቹ የአመራሩን ሥር ት ድክመቶች በዝርዝር በማንሳት መሻሻል እንዲኖር መክረዋል።

## የአገር ጠባቂ ጦር አመሠራረትና አደረጃጀት[19]

በታኅሣሡ ግርግር፣ የመፈንቅለ መንግሥቱን አራማጆችና የዘውድ ጠባቂውን ወገን ደግፎ የተፋለመው፣ ለመፈንቅለ መንግሥቱ አነሣስና አወዳደቅ ከፍተኛ ሚና የተጫወተው መለዮ ለባሹ ስለሆነ፣ የዚህን ልዩ ልዩ መለዮ ለባሽ ጦርና የፖሊስ ሠራዊት አመሠራረትና ሥልጠና ማወቁ የመፈንቅለ መንግሥቱን ሒደት ለማወቅ ስለሚረዳ እንደሚከተለው እዘረዝራለሁ።

በኢትዮጵያ በየዘመኑ የተነሡ ነገሥታትና ገዢዎች የአገሪቱን የውስጥ ፀጥታ ያስከበሩና የውጭ ጠላት ወረራንም ሲከላከሉ የነበረው ጦር፣ ጋሻ፣ ጎራዴና የተወሰነ ነፍጥ በያዙ ችግር ሲመጣ በሚሰበሰቡ እና ችግሩ ሲያልፍ ወደቀድሞ ተግባራቸውና ክልላቸው በሚበተኑ ገበሬዎች የሚገነባ ጦር ነበር። ከዚህ ሌላ፣ የነገሥታቱ ቤተ መንግሥትም ሆነ የባላባቱና የመኳንንቱ አምባ ይጠበቅ የነበረው በሰላሙ ጊዜ የዕለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን፣ በዘመቻ ጊዜ ደግሞ ስንቅ የሚሆን እህል የሚያገኝበት በርስትነትና በማደሪያነት በሚሰጥ መሬት በሚተዳደር ጦረኛ ነበር።

የኢትዮጵያ ጦር ምሥረታ ሲነሳ ስማቸው የሚነሣው ዐፄ ቴዎድሮስ ናቸው። ለዚህ ደግሞ የራሱ ታሪክ አለው። ከ፲፰ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ጀምሮ፣ አውሮፓውያን ከደረሱበት የሥልጣኔ ዕድገት ደረጃ አንፃር ኋላቀር የሆኑትን የዓለም ክፍል፣ በተለይም አፍሪካን የኢንዱስትሪ ውጤታቸው ማራገፊያ፣ የጥሬ ዕቃ ማፈሻ፣ እንዲሁም እርካሽ የሰው ጉልበት ማግኛ ለማድረግ ተነሳስተው ነበር። በዚህ መሠረት በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በቅኝ ግዛት ማካጣጠሪያ ቀለበት ውስጥ ከገቧቸው የአፍሪካ አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ስለነበረች፣ በተደጋጋሚ የውጭ ኃይሎች የጦርነት ትንኮሳ ተቃጥቶባታል። ይህ ጊዜ ደግሞ በአገር ውስጥ መሳፍንቱ የሥልጣን ሽሚያ ውድድር ይዘው አገሪቱን በአምባ በመከፋፈል እርስ በእርስ ከመዋጋት በቀር፣ በውጭ ወራሪ ሊቃጣ ለሚችል አደጋ ትኩረት የሚሰጥ ስላልነበረ የአገሪቱ ነፃነትና ሉአላዊነት ለብርቱ አደጋ የተጋለጠበት ጊዜ ነበር።

በወቅቱ ተፎካካሪዎቻቸውን በጦር ሜዳ ላይ ድል አድርገው ወደሥልጣን የመጡት ዐፄ ቴዎድሮስ የሁኔታውን አደገኛነት በመገንዘብ ማዕከላዊ መንግሥቱን ከተቆጣጠሩ በኋላ አገሪቱን በአምባና በጉጥ ከፋፍለው ይዘው የነበሩትን መሳፍንትና

[19] *እዚህ ላይ አንባቢያንን ማሳሰብ የምፈልገው፣ ይህ ርዕስ የኢትዮጵያን ነፃነትና አንድነት በማስከበር ለሕዝቡ ዕድገትና ብልጽግና መሠረት የሆነውን ሰላምና ጸጥታ ለማስገኘት ሁኔታው የጠየቀውን መስዋዕትነት ሁሉ እየከፈለ፣ የአገር መከታና የሕዝብ አለኝታ ሆኖ የኖረው የአገር ጠባቂ ጦር፣ ከአደረጃጀት ጀምሮ የሔደበትን ጉዳናና በየጊዜው የፈፀመውን ሥራ በዝርዝር የሚያስረዳ በጥልቅ ጥናት ላይ የተመሠረተና የተሟላ የአገር ጠባቂውን ጦርና የፓሊስ ሠራዊቱን ታሪክ ለማቅረብ ያለመ አይደለም። በዚህ ርዕስ የማቀርበው በ፲፱፻፶፫ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ውስጥ በስም የሚጠቀሱ የአገር ጠባቂ ጦርና የፖሊስ ሠራዊት ልዩ ልዩ ክፍሎች ስለሆኑ፣ እነዚህ መለዮ ለባሾች ለምንና እንዴት እንደተቋቋሙ፣ በእያንዳንዱ ድርጅት አመሠራረትና አደረጃጀት ላይ ልጽፍ ለተነሣሁበት ታሪክ የሚያስፈልግ አንዳንድ ጭብጥ ለማስያዝ ይረዳል ብዬ የመንኩበት አጭር መግለጫ ነው። የአገር ጠባቂ ጦራችን ሙሉ ታሪክ ወደፊት ተጽፎ እንደምናነብ ተስፋ አደርጋለሁ።*


መኳንንት፣ እሽ ያሉትን በሰላም፣ እምቢ ያሉትን በኃይል፣ እያስገበሩ፣ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት የምትመራ ጠንካራ ኢትዮጵያን እንደገና መመሥረትን ዐላማቸው አድርገው ነበር። ከዚህ ጋር በተያያዘም አገሪቱ ካንዣበበባት የውጭ ጠላት አደጋ ለመታደግ የሚችል ወታደራዊ ዐቅም እንዲኖራት፣ የራሷን መሣሪያም ለመሥራት እንድትበቃ ማድረግም የንጉሡ ዕቅድ ነበር። የራሷን መሣሪያ የመሥራቱ ጉዳይ ሲነሳ ዐፄ ቴዎድሮስ በተለይ አገር ውስጥ መድፍ ለማሠራት ያደረጉት ጥረት ተጠቃሽ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለዚህ፣ ስለዐፄ ቴዎድሮስ መድፍ፡ አንዳንድ ነጥብ ማንሣት ያስፈልጋል።[20]

መድፉ ሊሠራበት የታቀደበት የመጀመሪያው ቦታ ቀደም ብሎ ይታወቅ በነበረበት ስም በበጌ ምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት በስሜን አውራጃ "ድብ ባሕር" የተባለው አገር ነበር። ቦታው ፈላሾች (ቤተ እሥራኤሎች) የብረት እና የባሩድ ማዕድን አግኝተው የብረቱን አፈር እያቀለጡ ትናንሽ እንደ ገጀሞ፣ ካስማ፣ መኮትኮቻ፣ መጥረቢያ የመሳሰሉ የመገልገያ የብረት መሣሪያዎች ይሠሩበት እንደነበር የሚታወቅ ነበር። በአካባቢው አፈ-ታሪክ መሠረት ፖርቱጋሎች በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ይህን የቤተ እሥራኤሎችን አንዳንድ የጅ ሥራዎች ሲያዩ በቅናት ስማቸውን አጥፍተዋል። ስለፈላሻዎቹ የአካባቢውን ነዋሪ የሰበኩት «እነዚህ ብረት ሠራተኞች ቀጥቃጮች ዓይናቸው መጥፎ ነው። ልጆቻችሁን ካዩ ልጆቻችሁ ይሞታሉ። ስለዚህ በአካባቢያችሁ እንዳይኖሩ ማድረግ ነው» የሚል ነበር። በተለይ «እነዚህ ሃይማኖታቸው የተለየ ክፉዎች፣ ክርስቶስን የሰቀሉ የተረገሙ ናቸው። እኛ እንደ እናንተ ክርስቲያኖች ነን። ክፉ አናደርግም» ያሉት ሕዝቡን ስላሳመነው፣ (ፈላሾቹ) ቤተ እሥራኤሎች ከነበሩበት ሥፍራ በኃይል እንዲለቁ ተደርገዋል። የተለቀቀውን ቦታም ራሳቸው በመያዝ እንደቤተ እሥራኤሎቹ ትናንሽ የብረት መገልገያዎችን ይሠሩ እንደነበር ይነገራል።

እንደ አፈ ታሪኩ ዐፄ ቴዎድሮስ መጀመሪያ ቦታውን የመረጡት ይህን ታሪክ ሰምተው ነበር። ነገር ግን በቦታው የተገኘው የብረት ማቅለጫው ጋን (ፈርነሱ) የብረቱ አፈር ቀልጦ ማር መስሎ ከመፍሰሱ በፊት እየፈነዳ ስላስቸገረ፣ ለብረቱ ማቅለጫነት (ለፈርነስነት) ከዚህ የተሻለ አፈር በደብረ ታቦር አውራጃ ጋፋት በተባለው ቀበሌ አለ የሚል ዜና ሲደርሳቸው እዚያ ሙከራ እንዲጀመር ተደረገ። በጋፋት የተገኘው የብረት አፈር ማቅለጫ ጋን (ፈርነስ) መሥሪያው አፈር እንደተባለው ከድብ ባሕሩ የተሻለ ቢሆንም ለትንንሽ ብረት መሥሪያ የብረት አፈር ለማቅለጥ እንጅ ለትልልቅ ብረት መሥሪያ የሚሆን የብረት አፈር አቅልጦ ማር መምሰል ሲጀምር፣ አሁንም ጋኑ እየፈነዳ ሊቋቋመው አልቻለም። ተደጋግሞ ቢሞከርም ለውጥ ስላልተገኘ፣

[20] ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ መድፍ ያሰባሰብኳቸውን መረጃዎች ያገኘሁበት በ1960ዓ.ም. ወደአካባቢው ለጉብኝት ሌሎችንም አስተባብሬ መድፎቹ የተሠሩበት ቦታ ድረስ በመሔዴ ነው። የአካሔዱ ሁኔታና ጉብኝቱ ውጤት ወደፊት በቦታው የሚዘረዘር ይሆናል።


የብረት አፈር ማቅለጡ ሙከራ ቀርቶ ብረት፣ ነሀስ፣ መዳብ የሆኑ ቁሳቁሶች ከየመኪንንቱ፣ ከግለሰቦች እና አድባራት ተሰብስቦ መጥቶ የተደረገው የብረት ማቅለጥ ሙከራ አዋጭ ሆኖ ተገኝና ከዚህ በታች የሚታዩት መድፎች ተፈበረኩ።[21] መድፎቹ በቁጥር አሥር ናቸው ይባላል።






*ከተመረቱት መድፎች በከፊል*

■ *እነዚህ የዓፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ወይም የመጀመሪያ የዕንዱስትሪ ውጤት መድፎች ታላቅ የአገር ታሪክ ቅርስ ናቸው።*



ከተመረቱት መድፎች በከፊል

ከላይ ባለው ስለጉብኝቱ በሚያሳየው ፎቶ ላይ ከመድፉ ኋላ ጥቁር መነጽር አድርጎ የሚታየው ሰው[23] አገጭ ሥር ጧፍ የሚመስል ቋድ የተባለ ባሩድ ማቃጠያ የሚገባበት ቀዳዳ አለ። አቀራቀሩም፣ አስቀድሞ በመድፉ አፍ ማቃጠያው ወዳለበት የተወሰነ መጠን ባሩድ ገብቶ ይጠቀጠቃል፤ ቀጥሎ ካምሱሩ (ማቃጠያው) ይላካል፤ እንደገና የተወሰነ መጠን ባሩድ ይከተታል። ከዚያም ጨርቃጨርቅ፣ የባናና የብረት ቁርጥራጭ ተከቶ ይጠቀጠቃል። አሁንም በድጋሚ የተወሰነ መጠን ባሩድ፣ የጨርቃጨርቅ፣ የባናና የብረታ ብረት ቁርጥራጭ ገብቶ ይጠቀጠቃል። ለሦስተኛም እንዲሁ አፈሙዙ ጥግ እስኪደርስ ድረስ ይጠቀጠቃል። ከዚያ ለመተኮስ ካምስሩ/ቋዱ/ እየነደደ ሔዶ ባሩዱን እየጣጣሰ የብረታ ብረቱ ቁርጥራጭ ተወርውሮ ሒዶ ከደረሰበት ቦታ እንደዛሬው ክላስተር በምብ በመበታተን ጠላትን ይጎዳል።



*በጅሮንድ አባትሁን ወርቅነህ*


ዐፄ ቴዎድሮስ ካሠሯቸው መድፎች ትልቁ መድፍ አንድ ጊዜ ተተኩሶ በእንግሊዝ ጦር ላይ ከፍ ያለ ጉዳት እንዳደረሰ ይነገራል። በሁለተኛው ዙር ተኩስ የብረታ ብረቱ ቁርጥራጭ ባሩድና ባናው በኃይል ተጠቅጥቆ ስለከበደ ከምሱሩ ሊቀጣጠል ታፍኖ በመያዙ አረሩ ወደ ውጭ መውጣት ሳይችል ቀርቶ መድፉ ራሱ ፈነዳ ይባላል።[24] ስለዚህ ሁኔታ ለማረጋገጥ ብንሞክርም በጉብኝታችን ወቅት በመቅደላ የዚያን መድፍ ስብርባሪ አላገኘንም። አንዱ መድፍ በተኩስ ሲፈነዳ አሁን በመቅደላ ያሉት አራቱ መድፎች አፈሙዛቸውን የእንግሊዝ ጦር ወደመጣበት ወደ ምድላ ድላንታ እንዳዞሩ ተቀምጠዋል። እንደ አስጎብኚያችን አገላለጽ ሌሎች አራት ትናንሽ መድፎች ከዚያ ተነስተው ደሴ በልዑል አልጋወራሽ ቤተ መንግሥት መግቢያ በር ላይ ተጠምደው ይገኛሉ። ይህም ማለት ከፈነዳው መድፍ ጋር አሁን ለቅርስነት የቀሩት በድምሩ ዘጠኝ መድፎች ናቸው። በቁጥር ስለተጓደለው አንድ መድፍ ፋራውን ለማግኘት አልቻልኩም። ለማንኛውም የቴዎድሮስና የእንግሊዝ ጦር ፍልሚያ በታሪክ ጎትጉ በሚታወቀው መልኩ ተቋጨ። መድፎቹም የኢትዮጵያ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ

---

*ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ስላደረጉት ጦርነት ብዙ ጊዜ ደጋግመው የነገሩዋቸውን በቃል ይዘውታል።*

[23] *አቶ ሚሊዮን በደርግ አስተዳደር በጠቅላይ ሚኒስቴር የአስተዳደር ጉዳይ ኃላፊ የነበረው ሲሆን፣ በቅርቡ በሞት ተለይቷል።*

[24] *አስጎብኚያችን ግራዝማች እንደሻው እንደነገሩን፣*



*በጅሮንድ አባትሁን ወርቅነህ*

የማምረት ታሪክ ሲነገር የዐፄ ቴዎድሮስን ፋና ወጊነት ማሳያና የአገሪቱ ታሪክ ቅርስ ሆኑ::[25]

ሌላው የዐፄ ቴዎድሮስ ዐላማ ቋሚ አገር ጠባቂ ጦር ማቋቋም ነበር። እስከ ዘመናቸው በነበረው አመራር የአገር ጠባቂው ጦር፣ ጦርነት ሲኖር ከየአካባቢውና ከየአገሩ እየተጠራ የሚሰበሰብ የገበሬ ጦር ነበር:: በዚህ ዓይነት የሚሰበሰበው የገበሬ ጦር ለአስቸኳይ ዘመቻ የሚጠራ ሲሆን፤ እንደየወቅቱ ሁኔታ ትቶት ወደ መጣው እርሻው፣ አጨዳው ወይም ውቂያው እየተሳበ የጦርነት ተግባሩን በሙሉ ልብ እንዳይወጣ መሰናክል ይሆንበት ነበር:: ከዚህ ውጪ ገበሬው በዚህ መልክ በየጊዜው ለዘመቻ ሲሠማራ፤ ከአምራችነት ተግባሩ ለተደጋጋሚ ጊዜ በመለየቱ በአገሪቱ የእህል እጥረት ያስከትል ነበር:: እንዲህ ዓይነቱን ችግር የተገነዘቡት ቴዎድሮስ ከእነዚህ ችግሮች ነፃ ሆኖ መደበኛ ሥራው የአገርን ነፃነትና ዳር ድንበር ማስከበርና አንድነትን ማስጠበቅ የሆነ፣ በአዲስ ሥርዓት የተደራጀ ቋሚና ተወርዋሪ አገር ጠባቂ የጦር ኃይል ማደራጀት እጅግ አስፈላጊ ሆኖ አገኙት::

ቋሚ የአገር ጠባቂ የጦር ኃይል የማቋቋም ሐሳብ በመሠረቱ የሚደገፍ ቢሆንም፤ ለዚህ ጦር መተዳደሪያ የሚውል ጥሪት የማዘጋጀት ግዴታ አብሮ መምጣቱ አልቀረም:: በጊዜው ከደጃዝማች ውቤ በምርኮ የሚገኘው ገንዘብ ለዚህ ይውላል የሚል እምነት አድሮባቸው ነበር:: ነገር ግን የተገኘው ገንዘብ የታሰበውን ያህል የሚያራምድ ባለመሆኑ ሌላ መፍትሔ መሻት አስፈለገ:: ቴዎድሮስ፣ በመጀመሪያ የመጣላቸው አማራጭ ሐሳብ ግብሩን ከሕዝብ በገንዘብ መሰብሰብ ነበር:: ነገር ግን በወቅቱ ይህን ያህል የገንዘብ ሀብት ያለው ብዙ ሰው ስላልነበረ ይህም ሊያዋጣ የሚችል አማራጭ ሆኖ ሳይገኝ በመቅረቱ፤ በሐሳቡ መግፋት አልተቻለም:: ሦስተኛው አማራጭ ደግሞ፣ በነበረው የመሬት ሥሪት የአገሪቱ ሢሶ መሬት ባለድርሻ አወዳሽ (ቀዳሽ) ሲሆን ብዛቱ በእርሳቸው እምነት ከአስፈላጊው በላይ መሆኑና፣ አብዛኛው አምራች ሳይሆን በላተኛ መሆኑን በመገንዘብ፣ የዚህን ክፍል የመሬት ይዞታ ቀንሰው የሚገኘውን ትርፍ መሬት ላሰቡት ቋሚ ጦር መተዳደሪያ ለማድረግ ዐቀዱ:: ይህ ከይዞታው ሊነቀልና ሊጣበብ የታሰበው ክፍል ግን ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር ቅርብና ጥብቅ ትስስር ያለውና፣ በሕዝብ ዘንድም ተሰሚነቱ ከፍተኛ የሆነ ስለነበር፤ የእርሱ መከፋት የዐፄ ቴዎድሮስን ዙፋን የነቀነቀ ብርቱ ተቃውሞ አስነሳ። ምክንያቱም በእንዲህ ያለ ሁኔታ የተከፋው

[25] በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን አማጭ መቅደላ ላይ ወጥቶ እነዚህ መድፎችን በመጠቀም ችግር እንዳይፈጥር ካለበት ቦታ በሔሊኮፕተር ለማንሣት ተሞክሮ ነበር:: ነገር ግን የእያንዳንዱ መድፍ ክብደት ከፍ ያለ ስለሆነ ከዚያ ቦታ አንስቶ ለመውሰድ ባለመቻሉ አቅልጦ ከጥቅም ውጭ ማድረግ አስፈለገ:: በዚህ የተነሳ በጅሮንድ አባትኩን የተባሉ ሰው በመንግሥት ተልከው መቅደላ መጥተው መድፉን ሦስት ቀንና ሌሊት በእሳት ቢያጋዩትም ሳይቀልጥ ቂጡ ላይ የመንቃት ምልክት ብቻ ለጥቶ ሳይቀልጥ እንደ ቀረ ሲሉ በቂጡ ላይ የሚታየውን ምልክት እያሳዩ ግራዝማች እንደሻው አስረድተዋል:: እነዚህ መድፎች ዐፄ ቴዎድሮስ የቦር መሣሪያ በአገራቸው ለማሠራት መሞከራቸውን ለማሳየት ብቻ ሳይሆን፤ በአገሪቱ የቴክኖሎጂ ውጤትነት ተጠቃሽ ቦታ ይዘው እንደሚዘልቁ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል:: መድፎቹን በቦታው ተገኝተን የነበሩበትን ሁኔታ ስንመለከት ግን ማዘናችን አልቀረም:: ዐፄውን የተመለከቱ ሌሎች ጉዳዮችም በግዴለሽነት እንደተተዉ ዓይተናል:: ሁነቱ የታሪክ ባለውለታዎቻችን በአግባቡ ስለማንንከባከብበት ምክንያት ጥያቄ አእምሯችን ላይ መጫሩ አልቀረም::

ይህ ክፍል በሕዝቡ ውስጥ የተቃውሞ መንፈስ በማሰራጨት ዐፄ ቴዎድሮስ የነበራቸውን ድጋፍ አሳሳው። በመጨረሻም ከውጪ የመጣባቸውን ጠላት ባላቸው ኃይል ለመከላከል በመቅደላ አምባ ላይ በመወሰናቸው ለእንግሊዞቹ ጥቃት ተጋልጠው ድል እንዲሆኑ አስገደዳቸው። ይህም ቴዎድሮስ እንደለመዱት ጠላታቸውን በመስክ እንዳይገጥሙና በዙሪያ ገባው ሠራዊታቸውን እየከፋፈሉ በለመዱት የቆረጣ ውጊያ ሠራዊቱ እንዳይዋጋ ጦራቸው ድል ተነሳ። ስለዚህ ቋሚ አገር ጠባቂ ጦር የማቋቋሙ ጥረት ወደፊት ተራዘመ።

በዐፄ ቴዎድሮስ ተወጥኖ የነበረው፣ በማዕከላዊው መንግሥት የሚመራ ቋሚ አገር ጠባቂ ጦር የማደራጀቱ ዐላማ፣ እንደገና በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ተቀስቅሶ የገነት ጦር ትምህርት ቤትን በማቋቋም በተግባር ዋለ። የገነት ጦር ትምህርት ቤት በስዊድኖች አሠልጣኝነት ለሠራዊቱ አመራር ሰጪ መኮንኖችን ማሠልጠን ጀመረ። የገነት ጦር ትምህርት ቤት የዘመናዊ ወታደራዊ ዕውቀት እንደማናቸውም ትምህርት ዐላማ ተነድፎለት፣ ሥርዓትም ተበጅቶለት ስልት ተከትሎ የሚካሔድ ዘመናዊ ማሠልጠኛ ነበር።[26] በጦር ትምህርት ቤቱ በእጩ መኮንንነት ሊሠለጥኑ የገቡት ወጣቶች በዘመኑ ከነበሩት ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች የተመለመሉ ሲሆን፤ ይሰጥ የነበረውም ሥልጠና፣ የቀለም ትምህርትን፣ ወታደራዊ ሥነ ሥርዓትንና በመጠኑም ቢሆን መሠረታዊ ዘመናዊ ወታደራዊ ሳይንስን አጠቃሎ የያዘ ነበር። መልእክትና መረጃን በፍጥነት ለማድረስ እንዲያስችል መልእክት በሬዲዮ የማስተላለፍና የመቀበል ትምህርትም ከሚሰጠው የሥልጠና ዓይነት አንዱ ነበር። በዚህ አኳኋን በትምህርት ቤቱ በአንድ ዓመት ሠልጥነው በምክትል መቶ አለቅነት የተመረቁት የመጀመሪያዎቹ የጦር መኮንኖች፣ ጥቂቶቹ አዲስ ለውትድርና እየተመለመሉ የሚመጡትን ሠልጣኞች በማሠልጠን ሥራ ተመደቡ። ጥቂቶቹ ደግሞ በሁለተኛው ዙር የእጩ መኮንንነት ኮርስ የሚሳተፉትን ሠልጣኞች፣ እነርሱን ካሠለጠኗቸው የስዊድን መኰንኖች ጋር በመሆን እንዲያሠለጥኑ ተመደቡ።

የአገር ጠባቂ ጦር የማደራጀቱና የማሠልጠኑ ተግባር በዚህ መልክ በጅምር ላይ እንዳለ፣ ፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በመጀመሩ አገሪቱ ችግር ውስጥ ገባች። በዚህ ጊዜ በዘመናዊ ጦር ከሠለጠኑት ከፊሉ በማይጨው ጦርነት ተካፍለዋል፡፡ ከማይጨው ጦርነት በኋላ አገር ሲፈታም አንዳንዶቹ በየአገሩ ከነበሩት አርበኞች ጋር ተቀላቀሉ። ሌሎቹ ደግሞ በጥቁር አንበሳ ጦር ስም ተደራጅተው ተዋግተዋል፡፡ በኋላም ከውጊያና ከዕልቂት የተረፉት ተሰደው ሶባት ሱዳን ውስጥ የውትድርና ተሐድሶ ሥልጠና ወስደው እየታገሉ ከንጉሡ ጋር ወደአገር ገብተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ትግልና በታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የጦር ዕርዳታ፣ በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. የኢጣሊያ መንግሥት አስተዳደር እንደወደቀ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ እስከ ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. አጋማሽ ድረስ ሲጠበቅ የቆየው፣

[26] «እኔም ነበርኩ» በሌፍተናንት ጀኔራል ዐቢይ አበበ


ቢ.ኤም.ኤም.ኢ. (British Military Mission in Ethiopia) በተባለው በብሪታንያ መንግሥት የምሥራቅና የደቡብ አፍሪካ ጦር ነበር። በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. አጋማሽ ገደማ ኢትዮጵያ የራሷን ጦር መልምላና አሠልጥና ለማቋቋም ስትዘጋጅ፤ የጦር አባላቱ የተመለመሉት አብዛኛው ከተፈታው የኢጣሊያ ጦር ውስጥ ከነበሩትና ከከተማ ሥልጡን ልጆች በማውጣጣት ነበር። በዚህ መልክ ፲፮ ሻለቃ ጦር ተዘጋጀ። በአርበኝነት ከነበረው ሠራዊት ውስጥ ደግሞ ፳፫ ሻለቃ ጦር ተመልምሎ፣ ቀደም ብሎ የጦር ሚኒስቴር ወታደር ይባል ከነበረው ፲፮ ሻለቃ ጦር ጋር በድምሩ ፴፮ ሻለቃ ጦር ተደራጀ። ይህ ሠራዊት በብሪታንያ ተራድኦ ድጋፍ ሰጭነት ተደራጅቶና ሠልጥኖ ለዳር ድንበር ጥበቃና ለአገር ውስጥ ደኅንነት ሲባል በየጠቅላይ ግዛቱ ተመድቦ ተላከ። ይህን ሠራዊት የሚመሩ ዘመናዊ የጦር መኮንኖች ማፍራት ደግሞ አስፈላጊና ግዴታም በመሆኑ ከዚህ ሠላሳ ስድስት ሻለቃ ጦር ውስጥ ንቁ፣ ቀልጣፋና በመጠኑም ትምህርት ያላቸውን መርጦ ሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤቱን በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. እንደገና በማቋቋም በርካታ የበታች ሹማምንትን በመኮንንነት ማሠልጠን ጀመረ። ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጨማሪ ወታደሮችና መኮንኖችም እየታከሉበት የጦር ሠራዊቱ በቁጥር እያደገ እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ድረስ ግዳጁን ሲወጣ ቆይቷል።

ቀስ በቀስ የሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት ዕድገት በማሳየት የመኮንኖቹ ሥልጠና ደረጃ ስላደገ፤ በማንኛውም የሠለጠነ አገር የጦር መኮንኖች ከሚሠለጥኑበት ደረጃ ጋር አቻ ሆነ። የሐረር የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር መኮንኖች ማሠልጠኛም ተቋቁሞ ሠራዊቱን የሚመሩ በርካታ የጦር አዛዦች አሠልጥኖ ማስመረቅ ችሏል። ጦር ሠራዊቱ በወታደራዊ አቋሙ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ኅብረተሰባዊ ተግባሩም እየጎላ መጥቷል። የጦር ሠራዊቱ ዝነኛውን ‹‹የመቻል›› እግር ኳስ ቡድን በማቋቋም፣ ‹‹ወታደርና ዐላማው›› ጋዜጣን በማሳተም፣ በርካታ የሕክምና ባለሞያዎችን (ዶክተሮችን) በማበርከት፣ የቀላል መሣሪያ ጥይት ማምረቻ (ፋብሪካ) በማቋቋምና የራሱን የሙዚቃ ባንድና ሕዝብ መዝናኛ[27] በመመሥረት አገልግሎቱን አስፍቷል።

[27] በወቅቱ ዘሚል ጎራዴው የተባለውን ቀስቃሽና አንቂ ተወዳጅ ዜማ ለሕዝብ ያቀረበ ነበር።


## ክብር ዘበኛ ጦር

ከሠራዊቱ ብዛትና ከተቋቋመበት ዐላማ አንጻር በቅድሚያ የተጠቀሰው የምድር ጦር አመሠራረት ይሁን እንጂ፣ ራስ ተፈሪ በአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. ቀኛዝማች መኩሪያ ባንትይርጉ አዛዥነት የሚመራ፣ ቁጥሩ ሦስት ሺህ አምስት መቶ የሚደርስ የግል የክብር ማስጠበቂያ ጦር አቋቁመው ነበር። ራስ ተፈሪ የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣኑን ሲይዙ የዚህ ጦር ቁጥር ወደ አምስት ሺህ ደርሶ ነበርና፣ ንግሡ በኋላ የንጉሡ የክብር ዘበኛ ተብሎ ለብቻው ተደራጀ። ይህ ሠራዊት ከቀደመው የአባት ጦር አደረጃጀት የሚለየው በተወሰነ አካባቢ የሚኖር፣ በዘመናዊ ወታደራዊ ጥበብ የሠለጠነ መሆኑ ነበር። ይህ ጦር ኢጣሊያ በጫረችው የአገር ወረራ ጦርነት በማይጨው ዘመቻ ላይ ጀብድ ሠርቶ አሳይቷል።



*ክብር ዘበኛ ጦር*


ነፃነት እንደተመለሰም በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. በሻለቃ (በኋላ ሜጀር ጄኔራል) ሙሉጌታ ቡሊ አዛዥነት እንደገና ተቋቋመ። በሠራዊቱ ውስጥ የተካተተው ከማይጨው ዘመቻ በፊት የክብር ዘበኛ አባል የነበረና የጣሊያን ወታደር የነበረ ከአዲስ አበባ ከተማ የተገኘ ሥልጡን የከተማ ሰው ብቻ ነበር። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የቀለም ትምህርት መኖር ለተመልማይነት ግዴታ አልነበረም። በኋላ ግን በሠራዊቱ ውስጥ የቀለም ትምህርት ያለውና የሌለው እየተለየ ለሌለው ከውትድርና ሥልጠና ጋር የቀለም ትምህርት



*ክብር ዘበኛ ጦር*

ነፃነት እንደተመለሰም በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. በሻለቃ (በኋላ ሜጀር ጄኔራል) ሙሉጌታ

እንዲሰጥና ጊዜ ተይዞለት እንዲማር ተደረገ። ከዚህ በኋላ በክብር ዘበኛ ሠራዊት ውስጥ ራሱን ችሎ የማያነብና የማይጽፍ ወታደር አልነበረም። የክብር ዘበኛ ጦር ኃይል በአገሪቱ የምድር ጦር ውስጥ የሚጠቃለልና ደመወዙም ከሌላው የምድር ጦር አባል ጋር አንድ ቢሆንም፤ በመለዮ ልብሱ፣ በድርጎ[28]ውና በዕዝ ሰንሰለቱ ለየት ያለ ነበር።




*የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ሠራዊት ግርማ ሞገስ ባለው የክብር በዓል ልብስ*



*የክብር ዘበኛ ሠራዊት በውጊያ ልብስ*

[28] *ግምቱ ለባት ብር የሆነ ልዩ ልዩ የምግብ ፍጆታዎች በድርጎነት ስለሚሰጠው*



*የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ሠራዊት ግርማ ሞገስ*
*ባለው የክብር በዓል ልብስ*



*የክብር ዘበኛ ሠራዊት በውጊያ ልብስ*

እንዲህ እንዲህ እያለም ሠራዊቱን በቀጣይነት የሚያሠለጥኑና የሚመሩ መኰንኖች ማፍራት አስፈላጊና ግድ ሆኖ ስለተገኘ፤ በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. የክብር ዘበኛ ጦር መኰንኖች ማሠልጠኛ (ካዴት) ትምህርት ቤት ተቋቋመ። ለአሠልጣኝነት የተመረጡትም ስዊድኖች ነበሩ። የማሠልጠኛው ድርጅት በተቋቋመበት ዓመት ተመልምለው የመጡለትን ፩፻፳ (አንድ መቶ ሃያ) ወጣቶች ተቀብሎ በዕጩ መኰንንነት ማሠልጠን ጀመረ። ትምህርቱና ሥልጠናው በስዊድን የጦር አካዳሚ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት ሆኖ በወታደራዊ ሳይንስና በቀለም ትምህርት ከ፲፱፻፴፮ እስከ ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. የሦስት ዙር ሥልጠና ከሰጠ በኋላ ማሠልጠኛው ተዘጋ።

የክብር ዘበኛ ጦር ችሎታውን ያስመሰከረባቸው ዓለም አቀፍ አጋጣሚዎች ነበሩት። ከእነዚህ አንዱ በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. ደቡብ ኮርያ በሰሜን ኮርያ ስትወረር ወረራውን ለማቆም ጦር አዋጥተው ወደ ደቡብ ኮርያ እንዲልኩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለአባል አገሮች ባስተላለፈው ጥሪ ምክንያት ነው። ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል አገር በመሆንዋ የተጠየቀችውን የሰው ኃይል መዋጮ ለመላክ በጊዜው በወታደራዊ ሳይንስ ሥልጠናና በንቃተ ሕሊናው ከምዕራብ አገር ጦር ጋር የሚቀራረብ ነው ተብሎ ከታመነው ከክብር ዘበኛ ጦር፤ ከ፲፱፻፵፬ እስከ ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. አራት ዙር ዘማች ጦር በማከታተል ወደ ደቡብ ኮርያ ላከች። እያንዳንዱ ዙርም ፩ሺ፭፻ (አንድ ሺህ አምስት መቶ) ወታደሮችንና መኰንኖችን ያካተተ ነበር። ይህ ከ፩ኛ እስከ ፬ኛ ዙር የዘመተው ጦር ደቡብ ኮርያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ከ፲፮ አባል አገራት ከተላከ ጦር ጋር በመግባባት የዘመኑን የተዋጊነትን ስልት ከአባቶቹ ከወረሰው የጀግንነት ወኔ ጋር በማጣመር፣ የተላከበትን ግዳጅ በሚገባ የተወጣ ነበር። ጦሩ በዚህ ብቻ ሳይሆን፣ አብሮ ከዘመተው የአባል አገር ጦር ጋር ማከናወን ከነበረበት ወታደራዊ ግዳጅ በላይ ጀብድ በመሥራት አባሉን ከነሕይወቱ ቀርቶ ሬሳውን ያላስማረከ የተደነቀ ጀግና ሠራዊት መሆኑን አስመስክሯል።

ሌላኛው ገጠመኝ ደግሞ የክብር ዘበኛ ጦር ለዓለም አቀፍ ተልኮ ወደኮንጎ መሔዱ ነው። በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. ኮንጎን ከቅኝ ገዥዋ ከቤልጅግ ነፃ ለማውጣት አገሬው በፓትሪስ ሉሙምባ መሪነት ትግሉን ተያይዞ ወደ ግብ ለመድረስ መቃረቡን ሲያዩ፤ የምዕራብ አገሮች ሉሙምባ የፖለቲካ ዝንባሌው ወደ ምሥራቅ ያዘነበለ ይመስላል በሚል ጥርጣሬ ካዛቡቡና ኮሎኔል ሞቡቱ እንዲሁም ሞይዝ ቾምቤ እንዲቀናቀኑት በማስነሳታቸው፤ የኮንጎ ነፃ አውጪ ታጋዮች ከሁለት ተከፍለው በርስ በርስ ግጭት መተላለቅ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ብጥብጡን አስቁሞ ሕዝቡን የሚያረጋጋ ሰላም ጠባቂ (ወይም) ፖሊስ የሚሆን ኃይል ኢትዮጵያ እንድትልክ ጠየቀ። ኢትዮጵያም ፈቃደኝነቷን አሳወቀች። በዚህ ጊዜ ግን ቀደም ብሎ ኢትዮጵያ በኮሪያ ዘመቻ ጊዜ ከክብር ዘበኛ ብቻ በመላኩዋ በጦር ሠራዊቱ ክፍል

ቅሬታ ተፈጥሮ ነበርና፣ ይህን ቅሬታ ለማስወገድ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ከክብር ዘበኛ አንድ ሻለቃ፣ ከጦር ሠራዊት አንድ ሻለቃ ጦር ተዋጥቶ እንዲላክ አስደረገ::[29]



ሌተና ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ የኮንጎን ዘማች ጦር በአውሮፕላን ማረፊያ ሲሸኝ

## ገበያ ወጣህ ምን ይዘህ መጣህ?

ከመጀመሪያ እስከ አራተኛ ዙር ወደ ደቡብ ኮርያ ዘምቶ የነበረው የሠራዊት አባል ወደአገሩ የተመለሰው በተለያየ ምክንያት ከዘመቻ ግዳጅ ውጭ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወደ ኮርያና ጃፓን ከተሞች በመሔድ የከተሞችን ውበት፣ የሥልጣኔውን ምጥቀት፣ የሕዝቡን ኑሮ ዕድገት ከአገሩ ጋር እያወዳደረ "ለምን?" የሚል ጥያቄ በልቡ ተሰነቀረ:: በዘመቻው ጊዜና በእረፍት ጉብኝቶች ዘማቹ ያየውንና የሰማው ሁሉ ማብሰልሰሉ ወደአገር ሲመለስ ማኅበራዊ ግንዛቤውን እንዲያሰፋ አድርጎታል:: በተለይ የክብር ዘበኛ የሙዚቃ ክፍል[30] ከሕዝብ ጋር የሚያገናኝና የሚያቀራርብ ማኅበራዊ ግልጋሎት እየፈጠረ ብዙ ሕዝብ ከማስደሰትና ከማዝናናቱ በላይ፣ በሙያ ዘርፍም ሕዝባዊ አገልግሎት ለመስጠት ለሚደራጁና ለተደራጁ ቀስቃሽና አንቂ ኃይል እየሆነ

[29] ኮለኔል ጃገማ የመፈንቅለ መንግሥቱን ውጊያ አስመልክተው ለበላይ አለቆቻቸው ባቀረቡት ዘገባ ግን ኮሎኔል ወርቅነህ የጦር ሠራዊቱን ጥሩ ተዋጊ ክፍል ወደ ኮንጎ የላከው የመፈንቅለ መንግሥቱን ችግር ለማቅለል ነው ሲሉ ዘግበዋል::

[30] በደቡብ ኮርያው ዘመቻ ወደጃፓን ያቀኑት የክብርዘበኞች ገጠመኙን የሚያመለክተው


ሩቅ ምሥራቅ ላለሁ ጃፓኗን ወድጄ
ትዝ ትለኛለች በፍቅሯ ነድጄ

የተሰኘው የትዝታ ዘፈን የክብር ዘበኛ ሬድዮ ጣቢያ ከሌላው ሙዚቃ ጋር እያቀናጀ በሬዲዮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስደምጠው ዘፈን የብዙዎችን ቀልብ ይስብ ነበር::



*ሌተና ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ የኮንጎን ዘማች ጦር በአውሮፕላን ማረፊያ ሲሸኝ*

ምጣቱ፣ የክብር ዘበኛ ሠራዊት በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅና ተመስጋኝ ሆነ፡፡ ጠቅልና ራዊቱ የሬዲዮ ጣቢያ፣ ወታደርና ጊዜው ጋዜጣ፣ መኩሪያ ስፖርት ክበብ[31] ዚቃና ቲያትር፣ የፖሎ ጨዋታ (የፈረስ ገና ጨዋታ)፣ የፈረስ እሽቅድድም፣ ኩሪያ የእግር ኳስ ቡድንና የሰልፍ ትርኢት ዋና ዋና የሕዝብ መሳቢያ ተቋሞቹና ሎቶቹ ነበሩ፡፡



*የክብር ዘበኛ በሚያደርጋቸው ሰልፍ ከፊት ጂፕ ላይ ተቀምጦ የሚታየው አንበሳ ለአየር መንገዱ እንደማስታወቂያ እንዲሆንም ያገለግል ነበር፡፡*

የክብር ዘበኛ ሠራዊት የአስተዳደራዊና የማኅበራዊ ይዘቱን ዕድገት ከፍ ማድረግ፣ የመማር ፍላጐትና ብቃት ያላቸውን የሠራዊቱን አባላት በአዲስ አበባ ተማ በሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ማለትም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሌጅ በኤክስቴንሽን ክፍሉ፣ በሕንፃና መሐንዲስ ኮሌጅ በቀን ተማሪነት ገብተው ፍተኛ ዕውቀት ገብይተው በመመረቅ፤ ራሳቸውን፣ ሠራዊቱንና አገራቸውን እንዲጠቅሙ መንገዱን ሁሉ አመቻችቶላቸው ነበር፡፡ እንዲሁም ቁጥራቸው የማይናቅ ኮንንኖች የ፲፪ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና አልፈው ወደ ጐንደር ሕክምና ሳይንስ ሌጅ ከተደለደሉት ተማሪዎች ጋር አብረው ገብተው ለሦስት ዓመታት የሚሰጠውን የጤና መኮንንነት ትምህርት ተከታትለው እንዲመረቁም አብቅቷል፡፡ ከዚያም ወደ ዩጐዝላቪያ ተልከው ሙሉ የሕክምና ሞያ ትምህርቱን ጨርሰው በመመለስ ሠራዊቱና ለአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ የሕክምና አገልግሎት በመስጠት የሠራዊቱ ምና ክብር ከፍ እንዲል ረድተዋል፡፡ ከፊሉ ደግሞ ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት መግባት በኤሌክትሪክ፣ በአናጺነት፣ በመገናኛ፣ በመካኒክና በቀያሽነት ሙያ

[31] በአትሌቲክሱ እንደነ አበበ ቢቂላና ማሞ ወልዴ ያሉትን ሯጮችም ያበረከተ ሠራዊት ነው፡፡



*የክብር ዘበኛ በሚያደርጋቸው ሰልፍ ከፊት ጂፕ ላይ ተቀምጦ የሚታየው አንበሳ ለአየር መንገዱ እንደማስታወቂያ እንዲሆንም ያገለግል ነበር፡፡*

እየሠለጠኑ ሠራዊቱን በተፈለገው ሙያ ሁሉ ተሟልቶ እንዲገኝ አብቅተዋል። ሥልጡኖቹ ከሠራዊቱ ሲሰናበቱ ሠርተው ኑሯቸውን የሚደግፉበት ሙያ በመያዛቸው፤ ኩራቱ ለነሱ ብቻ ሳይሆን ይህ ዕድል ላልደረሰው የሠራዊቱ አባልም መቀስቃሸና አንቂ በመሆን የሠራዊቱን አባሎች ሥነልቦና ከፍ የሚያደርግ ሆኖ ተገኝቷል።

## የፖሊስ ሠራዊት አቋምና አደረጃጀት

አንድ አገር ሰላሙ የተረጋገጠ እንዲሆን ማዘጋጀት የሚኖርበት፣ አገርን ከውጭ ጠላት ለመከላከል የሚያስፈልገውን ኃይል ብቻ ሳይሆን፤ በሰላማዊ ጊዜ በአገር ውስጥ የሕዝብ ሰላምና ፀጥታ እንዳይታወክ የመጠበቅ፣ የአገሪቱን ኢኮኖሚ የሚጎዱ ተንኮለኞችን የመከላከልና የመሳሰለውን ተግባር የሚያከናውን ሰላማዊ ሠራዊትም ነው። ይህም በመሆኑ፣ የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር ዐፄ ምኒልክ "የምስጢር ዘበኛ» በሚል ስያሜ የተወሰነ የሰው ኃይል ያለው ድርጅት በ፲፱፻፮ ዓ.ም. አቋቁመው የሕዝቡን ሰላም ያስጠብቁ ነበር። የከተማው ነዋሪ በተለምዶ ከሚለብሰው ለየት ያለ ልብስና ቆብ የማያደርግ፣ በቆቡ ዙሪያ የምሥጢር ዘበኛ የሚል አርማ ቆየት ብሎ ደግሞ «ሰላም ጠባቂ» የሚል መለዮ ያደረገ የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ የሚያስከብር ኃይል አቋቁመው ያስጠብቁ እንደነበር ይታወቃል። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሥልጣን እንደመጡም፣ የሠራዊቱ ተግባር ያው ሆኖ ስሙ ያራዳ ዘበኛ ተብሎ ተለውጦ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ድረስ የሕዝብ ሰላም ሲጠብቅና ፀጥታ ሲያስከብር ቆይቷል። ጠላት ድል አድርጎ ሲገባ የአራዳ ዘበኛ ተቋም ፈረሰ። ይህን ተከትሎም የሠራዊቱ አባላት በየአገሩ ካሉ አርበኞች ጋር ተቀላቅለው ትግላቸውን ቀጠሉ። ከነርሱ መካከል የታወቁት ስመጥር አርበኛ የአራዳ ዘበኛው አዛዥ ያኔ ባላምባራስ (በኋላ) ራስ አበበ አረጋይ አንዱ ናቸው።

ጠላት እንደለቀቀና የኢትዮጵያ መንግሥት አስተዳደር እንደተቋቋመ ቀድሞ ያራዳ ዘበኛ ከነበሩት ጋር ሥልጡን የከተማ ልጆችን በመጨመር ከእንግሊዞች ጋር በመተባበር አዲስ የፖሊስ ሠራዊት ቀጥሮና አሠልጥኖ እስከ ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. አጋማሽ ድረስ ሲያገለግሉ ቆዩ። ከዚህ በኋላ ከሠራዊቱ መካከል መለስተኛ ኃላፊነት መቀበል ይችላሉ ተብለው የተገመቱ ጥቂት የበታች ሹማምንት ተመልምለው አመራሩን የሚይዙ መኮንኖችን ለማፍራት፣ የአጭር ጊዜ የመኮንኖች ማሠልጠኛ ተቋቁሞ ማሠልጠን ጀመረ። ትምህርት ቤቱ በሰው ኃይልና በማሠልጠኛ መሣሪያዎች አድጎና ተሟልቶ «አባዲና የፖሊስ መኮንኖች ማሠልጠኛ» ተብሎ ከየትምህርት ቤቱ በመጡ ወጣቶች ሥራ በመጀመር የፖሊስ ሠራዊትን የሚመሩ ብዙ መኮንኖችን አፍርቷል። ውሎ አድሮም ተቋሙ በኮሌጅ ደረጃ አድጎ «አባ ዲና የፖሊስ መኮንኖች ማሠልጠኛ ኮሌጅ›› ተብሎ ትምህርትና ሥልጠና ሲሰጥ ቆይቷል። ይህ ሠራዊት ግዳጁን ለመወጣት በአስፈላጊው ልዩ ልዩ የፖሊስ ሙያ የሠለጠኑ አባላት የተሟላ እንዲሆን በማሰብ፣ የፖሊስ ሠራዊት ወታደርና መኮንን ሥልጠና በሠፊው ተከናውኗል። በዚሁ

በፖሊስ ሠራዊት ድርጅት ውስጥ የተጠቃለለ፣ ሥራውና ኃላፊነቱ በፖሊስ ሠራዊት ጥላ ሥር ሆኖ ተግባሩና አሠለጣጠኑ ግን ለየት ያለ ፈጥኖ ደራሽ በሚል መጠሪያ የተደራጀ በኮሎኔል ታደሰ ብሩ (በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል) ይመራ የነበረ ኃይልም ተቋቁሞ ነበር። ይህ ሠራዊት ስሙ እንደሚያመለክተው፣ ለሚፈለግበት ተግባር ፈጥኖ በመድረስ ግዳጁን ለመወጣት የሚያስችል፣ ከክብር ዘበኛ ሠራዊት ወታደራዊ ሥልጠና ጋር የተቀራረበ ብቃት እንዲኖረው ተደርጐ የተዘጋጀ ኃይል ነበር። የዚህ ሠራዊት ይፋዊ ተግባርም አንዳንድ ከፖሊስ ሠራዊት አቅም በላይ የሆነ ኃይል የሚጠይቅ ፖሊስ ነክ ተግባር ሲያጋጥም፣ ፖሊስን መስሎ ማከናወን ሲሆን፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ፣ ከዚህ ወጣ በማለትም መለስተኛ የጦር ሠራዊት ተግባርን የማከናወን ግዳጅ የሚፈፅም ነበር።

የፖሊስ ሠራዊቱ በብርጋዴር ጄኔራል ጽጌ ዲቡ[32] መመራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከፍ ያለ የዕድገት ክንዋኔዎችን አድርጓል። ይህ ሊሆን የቻለው፣ አዛዡ ጄኔራሉ ከክብር ዘበኛ አዛዥ ከጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ጋር የቅርብ ጓደኛና የጠበቀ ወዳጅነት ስለነበራቸው፤ እየተመካከሩ ባወጡት ዕቅድ[33] መሠረት የፖሊስ ሠራዊት እንደ ክብር ዘበኛ ሠራዊት በአለባበስ፣ በንጽሕና፣ በወታደራዊ አቋም፣ በሕክምና ሞያ፣ በጋዜጣ ዝግጅት፣ በስፖርትና በሙዚቃ ... ወዘተ. ሙያዎች ተክኖ ሠራዊቱንና የአገሪቱን ሕዝብ ለማገልገል ስለቻለ ነበር።[34]

## የአየር ኃይል አመሠራረትና ዕድገት

ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯን ለማስጠበቅና ሉዓላዊነቷን ለማስከበር ከሚያስፈልጋት አገር ማስጠበቂያ ኃይል አንዱ የአየር ኃይል ተቋም ሲሆን የማደራጀቱ ተግባር የተከናወነው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። በመሠረቱ የአገሪቱ የአየር ኃይል አመሠራረት ረዘም ያለ ታሪክ ያለውና የበረራ ጥበብ ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ ጋር የሚያያዝ ነው። የዓለም አቭዬሽን ዕድገት ዛሬ ከሚገኝበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት የሰው ልጅ የመብረር ፍላጎት እውን ለማድረግ መስዋዕትነት የተከፈለባቸው አያሌ የበረራ ሙከራዎች ተከናውነዋል። አገራችንም የአውሮፕላን ጥበብ ግኝት ተጠቃሚ የሆነችው የመጀመሪያውን አውሮፕላን ነሐሴ ፲፰ ሁለተኛውን ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. ወደ አገሯ በማስገባት ነው።

---

[32] ለምርምር ይህን ሁሉ ውለታ የዋሉትን ጥሩ ኢትዮጵያዊ የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ፣ የጄኔራል ጽጌ ዲቡ የሕይወት ታሪክ ሰነድ አግኝቼ ለማካተት ከሚመለከተው ክፍል ሰነድ ለማግኘት ተደጋጋሚ ጥረት አድርጌ ሳይሳካልኝ ቀርቷል።

[33] ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. በወጣው ወታደርና ጊዜው ጋዜጣ የፖሊስ ሠራዊት ሙዚቀኞችን የክብር ዘበኛ ሙዚቀኞች ስለማሠልጠናቸው የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ ጄኔራል ጽጌ ዲቡ የሰጡት ምስክርነት እየተጋገዙ ለመሥራታቸው ማስረጃ ይሆናል።

[34] በሌሎች ግዜ የነበረው የባንዱ መሪ የሻምበል ሙዚቃውን (ማርሹን) ሲመራ ከጀርባው ላይ ይታይ የነበረው የኮቱ እንቅስቃሴ እጅግ በጣም ደስ የሚያሰኝ ስለነበረ እሱ ባንዱን እየመራ እስከድሙ ሲነሳ ሕዝቡ በሙሉ ተነስቶ በጭብጨባ ይቀበለው ነበር።



የአየር ኃይል

በኢትዮጵያ አውሮፕላን ለወታደራዊ ግዳጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰማራው መጋቢት ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ.ም. በራስ ጉግሣ ወሌና በጦር ሚኒስትሩ በደጃዝማች (በኋላ ራስ) ሙሉጌታ መካከል በተደረገው በአንችም ጦርነት ነበር። በኢትዮጵያ እነዚህ አውሮፕላኖች የማብረርና አስተዳደር ሥራ ኃለፊነት የወሰዱት መጀመሪያ ካፒቴን ማዬር የተባሉ የፈረንሳይ ተወላጅ ነበሩ። አውሮፕላኖቹ ‹ንስረ ተፈሪ›ና ‹ርግበ ተፈሪ› ይባሉ ነበር። ስዊዳናዊው ቮን ሮዘንና አሜሪካዊው ሮቤንስም የቀይ መስቀል አውሮፕላኖችን ይዘው በጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያ ገብተው የማብረሩንና የማስተዳደሩን ሥራ መርተዋል። ከጦርነቱም በኋላ ነጻነት እንደተመለሰ ተመልሰው መጥተው የተቋቋመው የአየር ኃይል አዛዥ በመሆን አገለግለዋል።

መደበኛው የአየር ኃይል ግንባታ የተፀነሰበት ጊዜ ነው ተብሎ የሚታመነው ግን ከእንግሊዝና ከአሜሪካ በተገኙ አውሮፕላኖች የበረራ ትምህርት የተጀመረበት ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. እንደሆነ የተለያዩ ጽሑፎችና የአየር ኃይሉ መጽሔቶች ይገልጻሉ። በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. ስዊድናውያን የበረራ አሠልጣኞች መጥተው ሥልጠናውን በስፋት የማካሄድ ተግባር ቀጠሉ። የበረራ ትምህርት ቤቱ በተቋቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራስን መቻል አብሳሪ የሆነው የበረራ ትርኢት በኢትዮጵያዊያን እጩ የበራ መኮንኖች ለመጀመሪያ ጊዜ መጋቢት ፳፮ ቀን ፲፱፻፵ ዓ.ም. ታየ። መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ.ም. ለመጀመሪያዎቹ እጩ መኮንኖች የምስክር ወረቀትና የአብራሪነት ምልክት የደረት ባጅ ተሰጡ። ከ፲፱፻፵፩ ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ ግን የአየር ኃይል ትምህርት ቤት በሁሉም ሙያዎች ለማሠልጠን የሚያስችሉትን የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች በማሟላት የራሱን የቴክኒክ ትምህርት ቤት አደራጀ። በመሆኑም እስከ ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ድረስ የሠለጠኑት ኢትዮጵያውያን የአየር ኃይል ባልደረቦች ያበሩዋቸው የነበሩት የተለያዩ ዓይነት ዘመናዊ አውሮፕላኖች ነበሩ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ወደ ጀት ዘመን በመሸጋገር፣ ጀት አውሮፕላኖች የሚያበሩ ኢትዮጵያውያን ፓይለቶችን በአገር ውስጥና ወደ ውጭ አገር ልኮ ማሠልጠን ያዘ። በዚህ አኳኋን ሥልጠናው ቀጥሎ፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከፍተኛ የአገር መከታነቱን ያሳመነና፣ በአፍሪካም አሉ ከሚባሉት ከሁለትና ሦስት ከማይበልጡ አገሮች በጥንካሬውና በተለይም በተዋጊ ጀት አብራሪዎች ደህንነት (SAFETY) እና በዒላማ ምት ተደናቂነትን ካገኙት የአፍሪካ አገሮች የአየር ኃይል ተቋማት አንዱ ለመሆን በቅቷል። እንዲህ በመሆኑ ከብዙ የአፍሪካ አገሮች የተላኩ የጦር ጄት አውሮፕላን አብራሪ ሠልጣኝ ፓይለቶችን ተቀብሎ እያሠለጠነ ለመመለስ በቅቷል።



*የአየር ኃይል*

ተፈሪ›ና ‹ርግበ ተፈሪ› ይባሉ ነበር። ስዊዳናዊው

## ሥርዓቱ የፈጠራቸው ችግሮች ተቃውሞ ስለማስነሳታቸው[35]

ከዚህ በላይ በአጭሩ እንደተጠቀሰው «ዘውዳዊው ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተሰጠና ዘር ግንዳቸው የሚገኝ ዘላለማዊ ውርስ ነው» በሚለው የነገሥታቱና የደጋፊዎቻቸው እምነትና አመራር ላይ የተመሠረተው የአንድ ሰው የፈላጭ ቆራጭ መንግሥት የሚፈፅመው የአስተዳደር በደል፣ የፍትሕ መጓደል፣ የአገር ሀብት ድልድል መዛባትና ሌላውም ሁሉ ተዳምሮ፣ ችግሩ ለአብዛኛው ሕዝብ ተሰማው፤ የበደሉ ብዛት እያደር እየበዛ ሲሔድ ደግሞ ወደ ዐመፅ ከመለወጡ በፊት መጀመሪያ ንጉሠ ነገሥቱን (ዘውዱን) በቀጥታ ሳይነካ በአስተዳደሩ (አመራሩ) ላይ ለውጥ ማስፈለጉ በተለያየ መንገድ ይገለጽ ጀመር። በዩኒቨርስቲ ኮሌጁ ውስጥም የታሪክና ሕግ መምራን የመሳሰሉት የሚያነሷቸው ፅንሰ ሀሳቦች ተማሪዎችን የዓለምና የኢትዮጵያ ሁነቶችን ለማነጻጸር ስለሚረዳቸው በወቅቱ በአገሪቱ ላይ የሚያዩትን የሕዝብ ችግር መነሻ በማድረግ በትምህርት በተገኘው የዕውቀት ብርሃን አማካኝነት በመፈተሽ ለማብሰልሰል ምክንያት እየሆነ ሔደ።

ወጣቱ ትውልድ ከፊሉ ለትምህርት፣ ሌላው ደግሞ ለሌላ ተግባር ወደ አንዳንድ በሥልጣኔ ወደገፉ አገሮች ሔዶ የማየት ዕድል ያጋጠመው ሲሆን፤ የቀረው ደግሞ ከሚያነበውና ከሌላም ምንጭ ከጨበጠው ግንዛቤ የተለያዩ አገሮች የአስተዳደር ሥርዓትን በአገሩ ካለው ኋላቀርና ጎታች ሥርዓት ጋር እያነፃፀረ ልዩነቱን በማውጣት ሥርዓቱን ለመለወጥ መታገሉ የሚጠበቅ ነው። ስለዚህ ወጣቱ የትግሉ ግምባር ቀደም ሆኖ መገኘት ግድ ሆነ። ይህ የወጣቱ ትግል ግን አንዳንዶችን ግር ማሰኘቱ አልቀረም። ተመልካችን ግር ያሰኘው ክስተትም የአገሪቱ ወጣት በትምህርትም ሆነ በንቃተ ኅሊና ደረጃ የተለያየ ከመሆኑ ባሻገር ከፍተኛ ትምህርቱን የተከታተለው በተለያዩ የአውሮፓና የአሜሪካ አገሮች እንደመሆኑ፣ ዐቋሙም በዚሁ ዓይነት ተለያይቶ ለአንድ ጉዳይ ባንድነት ለመቆም የሚቸግረው መሆኑ ነው። እንደዚያም ሆኖ ግን የአገሩ ኋላቀርነት ባሳደረበት ቁጭት ምክንያት ልዩነቱ ሳይገታው በሥርዓቱ ላይ በአንድነት ፅኑ ተቃውሞ ማስተጋባት ችሏል።

በእርግጥ የተቃውሞው እንቅስቃሴ መሠረት ሰፊ ነው። ክስተቱም እንደደራሽ ውሀ የመጣ ሳይሆን፤ በየጊዜው ሲያድግ የቆየ ነው። ለዚህ እንደምሳሌ ከሚጠቀሱት መካከል ቀደም ሲል ከንጉሡ ጋር በቅርብ ለመገናኘትና አስተሳሰባቸውን ለመረዳት ያጋጠማቸው ዕድል የንጉሡን ቅን ልቦና ዘላቂነት የተጠራጠሩ፣ እንደ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ያሉ ሰዎች ያካሔዱት ትግል አንዱ ነው። ደጃዝማች ታከለ ንጉሡ በመጀመሪያ ደረጃም ቢሆን አንዳንድ ጠቃሚ እርምጃ ሲወስዱ ይታዩ የነበረው ለውጭ ተመልካች ተራማጅ መስሎ ለመታየትና ለሕዝብ ይህን ያደረግንልህ ለውለታህ ነን እያሉ ውለታን በመቁጠር የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም እንጂ

[35] ወደቀደመ ነገሬ ስመለስ፤ የመንግሥቱን የአመራር ሥርዓት ቀጣይ ጉዞ የሚያመለክት ክፍል ነው።

መቼም ቢሆን ለአገር ዕድገትና ለሕዝብ ብልፅግና ዘላቂነት ያለው በጎ ስሜት አላቸው ብለው አያስቡም። ደጃዝማች ታከለ ዕድሜያቸውን ሙሉ ሥርዓቱን ሲታገሉ ኖረዋል። ደጃዝማች ታከለ "ኢትዮጵያን ሳልጎዳ ተፈሪን ማስወገድ ከቻልኩ ዋጋው የእኔን ሕይወት መክፈል ቢሆን እንኳ እከፍላለሁ"[36] በሚል ፅኑ ዐላማ ከጠላት ወረራ በፊት ጀምረው የንጉሡን ሥልጣን በሕግ ለመገደብ፣ ካልሆነም ንጉሡን በኃይል ከሥልጣን ለማውረድ ተደጋጋሚ ጥረት አድርገዋል። ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤም እንደዚሁ በሥርዓቱ ላይ ዐማፂ ነበሩ። ዮፍታሔ ንጉሤ የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን በሕግ የሚገድብ የሕገ መንግሥት ለውጥ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ሐሳቡ በሕዝቡ ዘንድ ሠርጾ እንዲገባና፣ ነገሩን እንዲያብሰለስል ለማድረግ የረዳ የንቃተ ኅሊና ማሳደጊያ ቅስቀሳ በማድረግ የለውጥ ሐዋሪያነት ተግባር የፈፀሙ ነበሩ።[37] ከዚህ በተጨማሪ የነበረውን ሥርዓት ለማስወገድ ጥረት ካደረጉት እነ ቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ፣ ዮሐንስ ረመሀ፣ አለቃ ፈጠነ፣ የሙሉ አለቃ በቀለ አናሲሞስ ... ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው።

ከቀጥታ ተቃውሞ ውጪ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሥርዓቱ ብልሹነት ምክንያት የሚደርስበትን በደል አጢኖ የራሱን እርምጃ እንዲወስድ ለማድረግ ተራማጆች የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅመዋል። ከመንገዶቹ መካከል በደራሲነት ሙያቸው በመጠቀም ያለው ሥርዓት ኋላ ቀርና ጉታችነቱን ሕዝቡ እንዲገነዘብ፤ ሌሎች አገሮች የደረሱበትን የሥልጣኔ ደረጃ በማሳወቅ ንቃተ ኅሊናውን በማዳበር ለዕድገት እንዲነሣሣና በአንድነት እንዲቆም ለማስተማር ጥረት ያደረጉም ነበሩ። ከነዚህ ውስጥ፣ ከበደ ሚካኤል፣ *ጃፓን እንደምን ሠለጠነች* እና *የዕውቀት ብልጭታ*፤ ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት፣ *አርአያ* እና *ቴዎድሮስ (ታሪካዊ ድራማ)*፤ ብላታ ሢራክ ኅሩይ፣ *ራስ ሴላስ* ... ወዘተ. በሥራዎቻቸው ያደረጉት አስተዋፅኦ ሳይነሣ የሚታለፍ አይደለም። በወቅቱ ድምፅ ማሰማት የጀመረው ጉዳቱ የነካው ሕዝብና አንዳንድ ተቆርቋሪዎች ብቻ አልነበሩም። ሁኔታውን በጥሞና ይከታተሉ የነበሩ አንዳንድ በንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ ሥልጣን የተሰጣቸውም ቅሬታቸውን ገልጸዋል። እነዚህኞቹ ሥልጣንንና ኃይልን በአንድ ሰው እጅ የመተውን አዝማሚያ አደገኛነት በመገንዘብ ሥርዓቱ በመፈንቀለ መንግሥት ከመገርሰስ ድኖ ቀስ በቀስ በሚደረግ የመሻሻል እርምጃ ወደሚፈለገው የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገር ለዚህም አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል። ለችግሩ መፍትሔነት እንዲረዱ መወሰድ ስለነበረባቸው አንዳንድ እርምጃዎች ከየአቅጣጫው የቀረበው ሐሳብና የተሰነዘረው አስተያየት ብዙ እንደነበር ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። እኔም እነዚህን በዝርዝር የማቅረቡን ኃላፊነት ለዘርፉ አጥኝዎችና ጸሐፊዎች በመተው፤ እዚህ ላይ ለተነሣሁበት ጉዳይ አስፈላጊ የሆኑ ጥቂት ማሳያዎችን ብቻ አነሳለሁ።

---

[36] *መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ፣ የአማርኛ ሰዋሰው መማሪያ መጽሐፍ*

[37] *- (በዜማ)"አንቺ ልጅ! አንቺ ልጅ!*
*ተክልከይ በዐዋጅ*
*ተክልከይ ተክልከይ ተክልከይ በዐዋጅ ሲሉ የተቀኙት የሚያመለክተው ይሔንኑ ነበር።*

## የውይይት መድረክ መዘጋጀት

[illegible]ካያዎቹ አንዱ በጊዜው ከመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አንዱ በነበሩት፣ በአቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ተወስዶ እንደነበር የሚነገርለት እርምጃ ነው። አቶ መኮንን የንጉሡን ታማኝና ዙፋኑ እንዳይነቃነቅ በከፍተኛ ንቃትና ትጋት የሚጠብቁ እንደነበሩ በጊዜው በነበረው ሁሉ በሰፊው ይታመንበት ነበር። የወጣቱ የፖለቲካ አዝማሚያ [illegible]ልፕ ወደ «ሥር ነቀል» ለውጥ (ሪቮሉሽን) ማዘንበሉን፣ በጎረቤት አገሮች በግብፅና [illegible] የታየው የመፈንቅለ መንግሥት እንቅስቃሴ ኢትዮጵያንም የሚያሳስብ መሆኑን [illegible] በማለት፣ የሚፈለገው ለውጥ እራሳቸው የቆሙለት የንጉሡ ክብርና ዙፋን ሳይነካ ሊመጣ የሚችልበትን ዘዴ ለማስገኘት በወቅቱ ከባድና ሊታሰብ የማይቻል ስልት ቀይሰው እንደነበር ይወሳል። ይህም ስልት የተማረው ወጣት እርስ በርሱ [illegible]ተገናኘ የሚመካከርበት መድረክ መፍጠር ነበር። በዚህ መሠረት መድረኩ ኢትዮጵያ ሀገር ፍቅር ማኅበር፣ የማታ ክበብ ተከፍቶ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ትምህርታቸውን የተከታተሉ ወጣቶች እየተገናኙ የሚነጋገሩበት እንዲሆን ተፈቅዶ ውይይቱ እንዲጀመር ማድረግ ነበር።

ስለዚህ የውይይት መድረክ መከፈት ሁለት አስተያየት ይሰጣል ። አንደኛው አስተያየት ሰውየውንና ጉዳዩን በቅርብ እናውቃለን ከሚሉ ሰዎች አዘውትሮ የሚሰማው ነው። እርሱም በአገሪቱ የአስተዳደር ለውጥ ሊገኝ የሚችለው "በሥር ነቀል" (በሪቮሉሽን) ብቻ ነው የሚል ዕምነት ያራምድ የነበረው የወቅቱ ወጣት ትውልድ፣ የመወያያ መድረክ አግኝቶ እርስ በርስ ሐሳብ በመለዋወጥ፣ ያለውን የለውጥ ፍላጎት ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችለው "በሥር ነቀል" (በሪቮሉሽን) ብቻ ሳይሆን፣ ሌላም ይህን ሐሳቡን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችልበት መንገድ መኖሩን እንዲረዳና እንዲቀይስ ለማድረግ የሚለው ነበር። ከዚህ ውይይት ሊመነጭ የሚችለው ሐሳብ የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋምን የሚጠይቅ እንኳን ቢሆን፣ ሐሳቡ በእሳቸው አማካይነት ለንጉሡ ቀርቦ በረጅም ጊዜ ሒደት፣ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈቀድበት ዕድል ሊኖር እንደሚችል ታስቦ እንደነበርም የሚጠቁም ነበር።

እንደ አስተያየት ሰጪዎቹ አቶ መኮንን የሥርዓት ለውጡ "በሥር ነቀል" "ሪቮሉሽን" ከሚሆን ደረጃ በደረጃ (በኢቮሉሽን) ቢከናወን፣ አገሪቱን የማይጐዳና እራሳቸው የቆሙለትን ዙፋናዊ አስተዳደርንም ጨርሶ ሳያፈርስ በማሻሻል ብቻ ሊካሔድ ይችላል የሚል እምነት እንደነበራቸው ያምናሉ። አቶ መኮንን ይህንን ማሰብ የደፈሩት ንጉሠ ነገሥቱ በሳቸው በኩል የሚቀርብን ሐሳብ ጎጂ አድርገው እንደማይቆጥሩት በመተማመናቸው ነበር።

ሁለተኛው አስተያየት ደግሞ ሰውየው መድረኩን ለመክፈት የተነሣሡት ለበጎ ዓላማ ሳይሆን፣ እራሳቸው ከፍተኛ የስለላ ሥራ ያካሒዱ ስለነበር፣ ወጣቱ መድረክ አገኘሁ ብሎ ተሰብስቦ በሚወያይበት ወቅት፣ ሐሳቡን በዚህ የስለላ መረባቸው አማካኝነት እያሰባሰቡ ለለውጥ የተነሣሣውን መንፈሱን ለማዳከምና ወጣቱን

ለመበታተን የሚቻልበትን እርምጃ ለመውሰድ ነው የሚል ነው ። ያም ሆነ ይህ፣ በመድረኩ የተገኘ ውጤት ስለመኖሩ የተገኘ ማስረጃ የለም።

የሰውየውን አገር ወዳድነት እናውቃለን የሚሉ የማይቀበሉት ቢሆንም፤ የመድረኩ መቋቋም ዐላማ እውነትም በሁለተኛው አስተያየት ላይ የተመሠረተ ነበር የሚለው ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልበት ዕድል ከፍተኛ ነው። ምክንያቱም ድርጊቱን ተከትሎ ለውጥ ስለመምጣቱ ምንም የሚጠቀስ ነገር ባለመኖሩ፤ መድረኩን ማዘጋጀቱ ወጣቱ በአገሩ ኋላቀርነት ያደረበትን ቁጭትና፣ ከዚህም በመነሣት ያሰላስል የነበረው ሐሳብና የፖለቲካው መገምሸር የወቅቱን አስተዳደር ሥጋት ላይ ጥሎት እንደነበር ለመጠቆም እንደማስረጃ ከማገልገል ያለፈ ጥቅም አልነበረውምና ነው። መቼም ተተኪው ትውልድ እኒህ ሰው ማን ነበሩ? ሥራቸው ምን ነበር? ብሎ መጠየቁ ስለማይቀር ስለ አቶ መኮንን ሀብተወልድ የሚከተለውን አጭር የሕይወት ታሪክ አቀርባለሁ።

## መኮንን ሀብተ ወልድ

መኮንን ሀብተ ወልድ የተወለዱት በ፲፰፻፺፪ ዓ.ም. አድአ ቢሾፍቱ ቃጅማ በተባለው ቦታ ነው። በተወለዱ በ፯ ዓመታቸው ዝቋላ ገዳም የአማርኛ ትምህርት መማር ጀምረው በ፲፭ ዓመታቸው ዜማና ቅኔ አጠናቅቀዋል። በ፲፱፻፫ እና በ፲፱፻፬ ዓ.ም. ዐፄ ምኒልክ ጤና በማጣታቸው በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጠበል ሲጠመቁ ለጸሎት መጽሐፍ አንባቢነት ወጣቱ መኮንን ሀብተ ወልድ በችሎታቸው ተመርጠው ለዐፄ ምኒልክ የጸሎት መጽሐፍ በማንበብ ሲያስታምሙ ለብዙ ቀናት ቆይተዋል። መኮንን ሀብተ ወልድ በተፈጥሮ ትጋትና ብርታትን የተጐናፀፉ ስለነበሩ፣ በ፲፱፻፲፪ ዓ.ም. ወደ መንግሥት ሥራ ከገቡ በኋላ በጉምሩክ ጸሐፊነት የጀመሩት አገልግሎት በልዩ ልዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጸሐፊነት፣ በዳይሬክተርነትና በዋና ዳይሬክተርነት እያገለገሉ ዘልቀውበታል። ጠላት ኢትዮጵያን ለመውረር በተነሣ ጊዜ፣ የሀገር ፍቅር ማኅበርን በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. አቋቁመው፤ ጠላትን የሚቃወም የፕሮፖጋንዳ ሥራ በመሥራት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል።



አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ



አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወደ ሰሜን የጦር ግንባር ሲዘምቱም በአዲስ አበባ የመንግሥቱ የፖለቲካና የፀጥታ ጠባቂ በመሆን፤ ከዚያም ጠላት ኢትዮጵያን ከወረረ በኋላ ወደ ፈረንሣይ አገር ተሰደው፣ ባሉበት አገር ስለ ሀገራቸው ነፃነት በተቻላቸው መጠን ልዩ ልዩ የፖለቲካ ሥራ ሠርተዋል። ከጠላት ወረራ በኋላ በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. የእርሻ ሚኒስትር ሆነው ሥራ ከጀመሩ በኋላ በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስትርነቱን ደርበው ይዘዋል። የእርሻ ባንክ ፕሬዚዳንትነትንም አብረው ይዘው ይሠሩ ነበር። በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም. የገንዘብ ሚኒስትር፣ ከዚያም የአገር ግዛት፣ እንደገና የንግድ የኢንዱስትሪና የፕላኒንግ ሚኒስትርና የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ፕሬዝዳንት ሆኑ። ከያዟቸው ሥራዎች ሁሉ በተጨማሪ ደግሞ የማስታወቂያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትን ይዘው በተጠባባቂነት ለአሥር ዓመታት መርተዋል። አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ በነዚህ ይፋ ሥራዎቻቸው ሳይወሰኑ፤ የንጉሠ ነገሥት መሥሪያ ቤቶች ላከናወኑት ሥራ ሁሉ የቅርብ ተመልካች ሆነው፣ በታማኝነትና በትጋት አገራቸውንና ንጉሠ ነገሥታቸውን እስከመጨረሻ ጊዜያቸው አገልግለዋል።[38]

ከአንዳንድ ዕርምጃቸው እንደሚታየው ግን አቶ መኮንን ዐላማቸውን ከሚጋሩ ሌሎች የመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር በግልና በጋራ እየሆኑ በወቅቱ አገሪቱ የደረሰችበትን የዕድገት ደረጃ ቀደም ካለው ዘመን ጋር እያነፃፀሩ ብዙ መሻሻል ተደርጓል በሚል ዕድገቱ (መሻሻሉ) ከዚያ ባለፈ ፍጥነት እንዳይራመድ ሲጥሩ፤ ሌሎች ደግሞ ተገቢውን እርምጃ የመውሰጃ ጊዜውን አዘግይቶ ብዙ ደም የሚያፋስስና የንጉሡን ታሪክ የሚያበላሽ አደጋ ከማስከተሉ በፊት እንዲታሰብበት የሚመክሩ እንደነበሩ በወቅቱ ይነገር ነበር። እነዚሁ ባለሥልጣኖች በመምከርና በማስጠንቀቅ ብቻ ሳይወሰኑ በጊዜው በሕዝብ ላይ በደል የሚያደርሰው ሥርዓት መሻሻል፣ ከዚያም እስከ መራራውን ሀቅ ተቀብሎ መለወጥና ሥልጣን የማካፈል ግዴታ እንዳለበት ደጋግመው አሳስበዋል። ዘግይቶም ቢሆን የመፈንቅለ መንግሥቱን እንቅስቃሴ መቃወም ተሰልፈው የነበሩ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት የሥርዓት ለውጥ እንዲደረግ ደግመው ደጋግመው ለንጉሡ ማሳሰባቸውን የሚገልጹ በርካታ መረጃዎች ተገኝተዋል።[39]

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የሥርዓቱ መሻሻል የግል ጥቅማችንን ይነካል ብለው የሚሠጉት የመሬት ከበርቴ፣ ልዑላን መሳፍንት፣ መኳንንት፣ ወይዛዝርትና የጥቅም ተጋሪዎች በቅንነት የቀረበን ገንቢ ሐሳብ ሁሉ በሥራ ላይ እንዳይውል «ይህ የሥልጣን ጥመኞች ፍላጐት እንጂ የሕዝብ ፍላጐት አይደለም» እያሉ መሰናክል መጋረጥ ዐቢይ ተግባራቸው ነበር። የሥርዓቱ ጠበቆች በለውጥ ፈላጊዎች የሚቀርቡ የማሻሻያ ሐሳቦችን ንጉሡ እንዳይቀበሉ ከሚያቀርቧቸው ማሳመኛዎች አንዳንዶቹ፣ ንጉሠ ነገሥቱ እንደማንኛውም ፈላጭ ቆራጭ መሪ ዝናና ምስጋናን መውደዳቸውን ግምት በማስገባት ነው። ሕዝቡ «ፀሐዩ ንጉሥ ለዘላለም ይኑሩ» ነው የሚልዎት፤

---

[38] አዲስ ዘመን ጋዜጣ ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ. ም.

[39] መፈንቅለ መንግሥቱ ትቶት የሔደው አሻራ በሚለው ምዕራፍ የተወሰኑትን ሐሳባቸውን ከመጠቃቀሴም በተጨማሪ ስለጉዳዩ የሚያስረዱ ሰነዶችንም በአባሪነት አያይዤአለሁ።

እንዲያውም ለእርስዎ ካለው ፅኑ ፍቅር የተነሣ አባቱን ትቶ በእርስዎ ስም «ኃይለ ሥላሴ ይሙት" እያለ ነው የሚምለው። ይህ ሁሉ፣ ሕዝብ የግርማዊነትዎን አመራር የሚወድ መሆኑን በግልጽ የሚያረጋግጥ ነው» በማለት ይሸነግላቸው ነበር። እነዚህ አባባሎች በዘመኑ መኖራቸው የማይካድ ቢሆንም፤ አመጣጣቸው ግን ከሕዝብ የመነጩ እውነተኛ የፍቅር መግለጫዎች ሳይሆኑ፤ በተለይ በወታደሩና በትምህርት ቤቶች፣ በሕዝቡም ዘንድ በመንግሥት ባለሟሎች ተሠራጭተው እንዲለመዱ የተደረጉ ናቸው። ወደኋላ ግን «ኃይለ ሥላሴ ይሙት!» ከሚለው መሐላ በስተጀርባ በወጣቱ ዘንድ እያደር ሲጠቀስ ይሰማ የነበረው በእውነት መማያነት ሳይሆን በእርግማን መልክ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም።

እነዚህ ከተለያዩ ሰዎች ይቀርቡ የነበሩ የአስተዳደር ማሻሻያ ሐሳቦች በሥራ ላይ እንዳይውሉ መደረጋቸው እውነትን መሸሽ ወይም ለመናገር ድፍረት የማጣት ልምድ ናቸው። በእርግጥ ንጉሠ ነገሥቱ ለሥልጣናቸው ከልክ ያለፈ ቀናኢ ስለነበሩ የማሻሻያ ሐሳብ ሲቀርብላቸው፤ የራሳቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውንና የቅርብ ወዳጆቻቸውን ጥቅም የሚነካ ሆኖ ካገኙት ወዲያው ውድቅ ያደርጉታል፤ አሊያም መልስ ነፍገው ያጠነዙታል። ይህም ሆኖ፣ አንዳንድ የአገሪቱን ፈርጀ ብዙ ችግሮች የተገነዘቡ አገር ወዳድ ሰዎች እርምጃው በንጉሡ ዘንድ ያላቸውን ቀረቤታና ታማኝነት ሊያሳጣቸውና ከዚያም አልፎ ጉዳት ሊያስደርስባቸው እንደሚችል እያወቁ፣ ይህን አልፈው ችግሩ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችልበትን መንገድ እየፈለጉ ለንጉሡ በማቅረብ ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ሲሉ ራሳቸውን ለመሥዋዕትነት እስከማቅረብ የደረሱ ነበሩ። ከእነዚህ መካከል እኔ የማውቃቸውንና የዚህ መጽሐፍ ትኩረት የሆኑትን ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ፣ ገርማሜ ንዋይና ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁን አነሳለሁ።[40]

[40] ብዙ ሰዎች የጀኔራል ጽጌ ዲቡን አንዱ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪ አድርገው ስለሚቆጥሩ ስለሙከራው ሲያወሱ ከመሪዎቹ ጋር በአንድ ላይ ይጠቅሷቸዋል። እኔ ይሔ ትክክል ነው ብዬ አላስብም። የጀኔራሉ ተሳትፎ በምን ደረጃ እንደሆነ ወደፊት የምጠቅሰው ስላለ ከመሪዎቹ ጋር ታሪካቸውን ለማካተት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም። በሚመሩት ሠራዊት ውስጥ ስላደረጉት አስተዋፅኦ እንኳን ዘርዘር አድርጌ ለማቅረብ ያደረኩት ጥረት እንዳልተሳካልኝ ከዚህ በፊት ገልጬዋለሁ።